

ፎቶ [illegible] 0911 42 92 83

## መልአከ መንክራት ግርማ ወንድሙ

‹‹በእርሱ ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ፤
ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ እንድናገለግለው ሰጠን፡፡››
ሉቃ.1፡74



# በማለዳ መያ’ዝ

## የክፉ መንፈሶች ድርጊት፣ ቅጽ - ፩

ከ______________________________

ለ______________________________

______________________

በመልአከ መንክራት ግርማ ወንድሙ
መጀመሪያ በመስከረም 2005 ዓ.ም ታተመ፡፡
አዲስ አበባ

3.2 በማለዳ እንገድለዋለን ........ 178
3.3 እንደገና ወደ ሸለቆ ........ 182

## ምዕራፍ አራት

4. የስደተኞች መንደር (አዶሉም) ........ 198
4.1 የይሁዳ እናት ልያ ........ 199
4.2 ሮቤል ........ 207
4.3 ይሁዳ ........ 207
4.4 የክፋት ልጅ ........ 222
4.5 መንቻካና ግትር ልጅ ........ 223
4.6 ክዚብ (የውሸት አገር) የተወለደ ልጅ ........ 224
4.7 መደባለቅና መደበላለቅ ........ 225
4.8 ትዕማር የአባቷን ቤት አገኘች ........ 233

## ምዕራፍ አምስት

5. በትልቅነት ውስጥ ያለ የአዙሪት መንፈስ ........ 248
5.1 የአዙሪት አምላክ ብኤልዜቡል ........ 251
5.2 የእግዚአብሔር መልአክና ኤልያስ ........ 254
5.3 በትልቅነት ውስጥ ያለ የአዙሪት መንፈስ ትውልድን ሲጥል ........ 264
5.4 ሜምፊቦስቴ የሸሸት ዘመን ልጅ ........ 273
5.5 የተሰበረውን መፈለግ ........ 277

## ምዕራፍ ስድስት

6. ትንሹ ልጅና የዘመኑ መንፈስ ........ 288
6.1 መከፈልና መከፋፈል ........ 288
6.2 ማባከንና መበተን ........ 292
6.3 ሁሉንም ከሰረ ........ 294





6.4 መዳበል ........ 299
6.5 ወደ ልቦናው መመለስ ........ 302

## ምዕራፍ ሰባት

7. ምነው ተኛተሃል? ........ 307
7.1 ከእግዚአብሔር ፊት መሸሽና በገንዘብ መመካት ........ 308
7.2 መጀመሪያ መውረድ- ውጣ የተባለው ወረደ ........ 310
7.3 ሁለተኛ መውረድ - ያለውንና የያዘውን ማራገፍ ........ 314
7.4 ሶስተኛ መውረድ - በሰው እጅና በተፈጥሮ ላይ መውደቅ ........ 319
7.5 አራተኛ መውረድ - በአውሬ ሆድ ........ 320
7.6 የባሕር ውስጥ ጩኸት ........ 321

## ምዕራፍ ስምንት

8. አምልኮት የሌለበት አገልግሎት ........ 325
8.1 ለራሱ መልስ የሌለው አገልግሎት ........ 327
8.2 አምልኮት ........ 330
8.3 ራእይ ........ 333
8.4 ሰማያዊ አምልኮትና የቅድስና ምስጋና ........ 334
8.5 ትውልድ ሲበላሽ የማያይ አገልግሎት፤ ........ 340
8.6 የድፍረት አገልግሎት፤ ........ 343
8.7 የእግዚአብሔር ቃል የማይሰማበት አገልግሎት፤ ........ 345
8.8 አምልኮት በሌለበት አገልግሎት ውስጥ የእርግማን መከሰት ........ 347
8.9 የዔሊ ዘመን ፍጻሜ ........ 350
8.10 የተሸነፈ ትውልድ ........ 352
ማጠቃለያ ........ 357

## ማስገንዘቢያ

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፤» ሮሜ. 8፡1

## ይህን መጽሐፍ ስታነቡ የሚከሰቱ ሁኔታዎች

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በስፋትና በጥልቀት የተጠቀሱት ትምህርቶች በሙሉ፤ ክፋውን መንፈስ በእጅጉ የሚያስቆጡትና የሚረብሹት በመሆናቸው፤ መጽሐፉን የሚያነቡ በተለይም የተደበቀ መንፈስ በውስጣቸው የሚገኝ ወገኖች ሁሉ፤ የሚከተሉት ሁኔታዎችና ጠባያት ይታይባቸዋል።

በዚህም ክፋውን መንፈስ ለመዋጋት፤ በቅድሚያ መንፈሱ በውስጣቸው መኖር አለመኖሩን ለማወቅ፤ ይህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ደረጃ እገዛ ሊያደርግላቸውና አንዳንድ ቀጥተኛ ምልክት ሊሰጣቸው እንደሚችል በትህትና ለማስገንዘብ እወዳለሁ። የሚታዩትም ጠባያት፤

- መደበት፣ ማዛጋት፣ ማንቀጥቀጥ፣ ማንጠራራት፣ ማልቀስ፣ ሳያውቁት እንባ መፍሰስ፣ ሰውነትን ማቃጠል፣ መውረርና መዘግነን፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ እያነበቡ መደናገር፣ በዓይንና በፊደላቱ ላይ ብዥታ መፍጠር፣ ግንባርና ዓይን ላይ የእንቅልፍ ማንገላጀጅና መጫጫን፤ የራስ ምታትና የሆድ ዕቃ መታወክ፤ በፍርሃት መጨነቅና የልብ ምት መጨመር፤ በአጠቃላይ መተከዝና መረበሽ በተደጋጋሚ መከሰት፣
- እንዲሁም በውስጥ የሥነ-ልቦና ግንዛቤ፤ ምትሃታዊ ድርጊት አደርጎ መገንዘብና በራስ ሕልውና ውስጥ ስለመንፈሱ አካሄድ መረዳትና ማወቅ እንዳይኖር ማከላከል፤
- የፍልስፍና፣ የርዕዮተ ዓለም ንድፈ ሐሳብና የሥነ - እውቀት አምልኮት የያዛቸው ሰዎች ደግሞ፤ ግራ በመጋባት፤ ሳይኮሎጂካል አካሄድ ነው፤ በማለት፤ ስለ ክፉው መንፈስ ጥቃት ላለመገንዘብ በር መዝጋት፤





- በክፉው መንፈስ ድርጊት ውስጥ ያሉ ደግሞ፤ ልዩ ልዩ የተቃውሞ መንገዶችን መጀመር፣ መቅበጥበጥ፤ መበሳጨትና መናደድ፣ ጥርስ መንከስ፣ መራገም ወዘተ... የመሳሰሉት ክፉ ጠባዮች ሁሉ፤ የምስጢሬ ወጣ ቁጭት መቀስቀስ ዋንኛው ክስተት ነው፤
- በንባብ ወቅት መንፈሱ የመንፈሱን የአያያዝ፣ የአኗኗርና የጥቃት ሥልቱ ምስጢራዊነት ሲገለጥበት፤ በውስጣቸው የተሰወረባቸው ሰዎች ያልሆነ ድምጽ ማሰማት፤ ድንገት መጽሐፉን መወርወር ወይም መደበቅ፣ መጮኽና እያነበቡ በከባድ እንቅልፍ መወሰድም፤ በተከታይ የሚጠበቅ ሂደት ነው፤
- ከዚህም በላይ ረጅም ዘመን የቤተክርስቲያን ልጅ ነኝ ብለው የሚመጻደቁ ሁሉ፤ በድንግዝግዝታ እንደኖሩበት ዓይነት የትዕቢት ዘመን፤ አጨልሞ ማየትና አቃቂር ማውጣት፤

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ሁሉ፤ ከሰዎች ክፉ ጠባይ ጋር ተደምሮ እንደሚቀርብ የሚጠበቅ መሆኑን አምናለሁ። ምክንያቱም መጽሐፉ በአምልኮተ እግዚአብሔር፤ በጸሎት፣ በስግደትና በሚስጢረ ቁርባን ውስጥ፤ የክርስቶስ ኃይል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንዲቀድም ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት፤ በክርስቶስ ሥጋና ደም ዕርዳታ ውስጥ የተዘጋጀ ስለሆነ፤ ዓለምና የዲያብሎስ ልጆች እንዲሁም ሳጥናኤልና ሠራዊቱ መበርገግ ሊከሰት የሚችል ግዴታ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን፤ እኔ ለክርስቶስና ለክርስቶስ ቤተክርስቲያን ኃጢአተኛ ባሪያው እንጂ፤ ከራሴ ሕይወት ምንም የለኝም። የሚያስገርማችሁ ነገር ቢኖር ግን « በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን! » ሮሜ. 8፡37

## የሕይወት መመሪያዬን ልጋብዛችሁ

«ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፤ ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል።» ማቴ. 6፡33

## መቅድም

### መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤

‹‹ በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላዕክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላዕክቱ ጋር ተዋጋ፣ አልቻላቸውም፣ ከዚያ ወዲያ በሰማይ ሥፍራ አልተገኘላቸውም። ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፣ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ፤ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላዕክቱም ከእርሱ ጋራ ተጣሉ። ታላቅ ድምጽ በሰማይ ሰማሁ። እንዲህ ሲል አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግስትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ። ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአል። እነርሱም ከበጉ ደም የተነሳ፣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሳ ድል ነሱት፣ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም። ስለዚህ፣ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፣ ደስ ይበላችሁ፤ ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፣ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።››

<u>ራእይ፡ ምዕ. 12÷7-12</u>





ከዚያ በኋላ፤ ዲያብሎስ በዓለም፣ በምድርና በሰው ልጅ ውስጥ አደረ። የሰው ልጆችም ከሰማይ ከተጣለው ከዚህ ሰይጣን ጋር ተባባሪ ሆነው ፈጣሪ አምላካቸውን እግዚአብሔርን አሳዘኑ።

በዚሁ መሠረት ዲያብሎስ በተገዙለት ውስጥ ሁሉ ገብቶ እየተንቀሳቀሰ በሚከተሉት የማጥቂያ መንገዶቹ አማካኝነት የክፉ ሥራውን ዘር ሲዘራ፤ የሕብረተሰቡን የአስተሳሰብና የዘመኑን ንድፈ-ሐሳብ ዕድገት በመከተል፤ አምልኮተ-እግዚአብሔርን በካዱና መንፈሳዊ ጉልበቱን በናቁ ሰዎች ላይ እያደረ፤ የዘር ልዩነትና የጎሣ ግጭት እየፈጠረ፤ በሃይማኖት ላይ የጥላቻ ዘመቻ በማካሄድ፤ በሥር ነቀል ለውጥ መንፈሳዊ ታሪካችንን ለማውደም፤ በክፉዎች አማካኝነት እየሠራ፤ የገንዘብ ትርፍና የማቴሪያል አምልኮት፣ የሥልጣንና የጉልበት ትልቅነት ትዕቢት እንዲፈጠር ከማድረጉም በላይ፤ በጤናው ረገድም ከፍተኛ ጥቃት አድርሶ፤ ዛሬ ወገኖቻችን፤ በየጠበሉ ቦታ፣ በየሆስፒታሉና በየጤና ጣቢያው ወድቀው ማየት የተለመደ ሆኗል።

ክፉው መንፈስ የቱን ያህል በረቀቀ ጥቃት ጉዳት እየፈጸመ መሆኑን በዚህ ድርጊት ልንገነዘብ ይገባል።

የዛር፣ የዓይነ-ጥላ፣ የመተት፣ የጥንቆላ፣ የዓውደ ነገሥት (የኮከብ ቆጠራ)፣ የሞራ ገላጭ፣ የእጅ መዳፍን የማንበብ፣ የሟርት፣ የባዕረ ሞት፣ የመናፍቅ፣ የደም፣ የሌባ፣ የዝሙት፣ የአስማት፣ የአፍዝ አደንግዝ፣ የጸብ፣ የሞገደኝነት፣ ያለመታዘዝ፤ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የሱስ፣ የፍልስፍናና የሥነ-ልቦና መንፈሶች ወዘተ... በዋናነት የሚጠቀሱ የዲያብሎስ የመግቢያና የማጥቂያ መንገዶቹ ሆኑ።

‹‹ ብዙሃን እለ ይቤሉ መኑ ያርእየነ ሠናይቶ፤ ተዐውቀ በላዕሌነ ብርሃነ ገጽከ እግዚኦ። » መዝ. 4÷6

‹‹በጎውን ማን ያሳየናል የሚሉ ብዙ ናቸው። አቤቱ የፊትህ ብርሃን በላያችን ታወቀ።››

የዚህ ዝግጅቴ ዋንኛ ዓላማ፤ በመጽሐፈ ኢያሱ፤ 3÷5 ላይ **‹‹ኢያሱም ሕዝቡን፦ ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገርን ያደርጋልና፤ ዛሬ ተቀደሱ አለ፤››** ባለው መሠረት፤ ድንቅ የማዳን ሥራውን ለዓለም ለማሣየትና የቤተክርስቲያናችንንና የክርስቲያኖችን መንፈሳዊ ኃይል ለማሣወቅ፤ ከመቀደስና ቅድስና መነሳት እንዳለብን ለማስገንዘብ እንዲሁም፤ የዲያብሎስ ውጊያ ምን እንደሚመስል በማሳየት፤ ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሁሉ፤ ዛሬ ከዘመኑ ሥልጣኔና የቴክኒዎሎጂ ዕድገት ጋር ጥበባቸውን አብረው እያሻሻሉ የመጡትን የክፉ መናፍስቱን ምንነትና፣ ከወቅቱ ጋር የሚራመድ ፈጣንና ተለዋዋጭ ሥልቶቻቸውን፤ እንዲሁም፤ አውዳሚ ጠባያቸውን ተረድተውና በኦርቶዶክስ እምነታቸው ጸንተው፤ የዲያብሎስን ውጊያ ያመክኑ ዘንድ፤ እገዛና ምክር ለመስጠት ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ይህ መጽሐፍ እስከ አሁን ድረስ የዲያብሎስ መንፈሶች በሕይወታችን ላይ ያደረሱብንን ጉዳቶች፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር በማገናዘብና በማያያዝ፤ ወደፊት የእግዚአብሔር አምላክ ልጆች ልንሆን የምንችልበትን አቅጣጫ በመጠቆም በኩልም፤ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርግ ነው።

በዚህ አቅጣጫ መንፈሳዊው ጉዞዋችን ፍሬያማ እንዲሆን፤ የወንጌል ስብከቱንና የፈውስ አገልግሎቱን ለማመቻቸት፤ በኦርቶዶክሳዊ እምነት ጸንቶ በመቆም፤ ብዙ መሰናክሎችንና እንቅፋቶችን ጥሎ በማለፍ፤ በተቻለ መጠን የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል ሁሉም ወገን እንዲያየው ለማድረግ ተችሏል።

እነኚህን የእግዚአብሔር ተአምራትንና እውነቶችን አምኖ መቀበልና አለመቀበል የእያንዳንዱ ግለሰብ ጉዳይ ቢሆንም፤ የወንድሞቻችን ከሳሽና የሰው ልጆች የቀደመው ጠላት ዲያብሎስ፤



በኃያሉ አምላካችን በእግዚአብሔር መንፈስ፤ የእያንዳንዳችንን ኃጢአት ይቅር በሚለንና በደሙ ቤዛነት በሚታደገን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፤ የዓለም መድኃኒታችንን በወለደችልን፤ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፤ እንዲሁም፤ በቅዱሳን መላዕክትና በጻድቃን ሰማዕታት ስም እየተገሰጸና አፍራሽ ተግባሩ ተይዞ ወደ ሲኦል ወርዶ ሲታሰር፤ የማዳን ጸጋውና ምሕረቱ ሲገለጥ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል በገሃድ የታየ መሆኑን ለመመሥከር እችል ዘንድ፤ የጥንታዊቷንና ገናናዋን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችንን ደንብና ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ፤ ይህንን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ተገድጃለሁ።

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው፤ ክርስቲያን ወገኖች ሁሉ፤ መንፈሶችንና መናፍስታዊ ድርጊቶችን በመመርመር፤ የእግዚአብሔርን ሙሉ ትጥቅ ታጥቀው ዲያብሎስን በመዋጋት፤ ትክክለኛው የአምላክ መንገድ ላይ እንዲገኙና እንዲራመዱ በማድረግ ረገድም፤ ይህ መጽሐፍ የጎላ አስተዋጽዖ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ።

በመሆኑም፤ የዚህ መጽሐፍ ዓብይ ርዕስ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠውን የሶምሶንን ታሪክ መነሻ በማድረግ፤ አዘጋጅቼዋለሁ።

በመጽሐፈ መሣፍንት ቁጥር አሥራ ስድስት መጀመሪያ ላይ፤ ሶምሶን ጋዛ መግባቱን የሰሙት የፍልስጥኤም መኳንንቶች ከተማዋን ከበው፤ መግቢያና መውጫያዋ ላይ አሸምቀው ‹‹በማለዳ እንገለዋለን›› በማለት፤ ሌሊቱን ሁሉ በዝምታ ተቀመጡ ይላል።

ቃሉ እንደሚነግረን፤ የፍልስጥኤማውያኑ መንፈስ ዕቅድና ፍላጎት፤ መጀመሪያ ሶምሶን በማለዳ ይዘው፤ ቀጥሎም ለመግደል ነው። ከዚህ እውነታ ስንነሳ፤ የእግዚአብሔር አምላክ ሰማያዊ ቃሉ ለልቦናችን እንደሚገልጸው፤ ጠላት ሁልጊዜ እኛን ለማጥፋት የሚያደባው በማለዳ መሆኑን ነው።

በመንፈሳዊው የእግዚአብሔር መንገድ ሳይሆን፤ በተጨነቁ በሽተኛ ሰዎች ሕሊና ውስጥ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ መንፈሶችን በምትሃት ኃይል በመላክ፤ ሥነ-ልቦናዊ በሆነ መንገድ የሚሠራ አደገኛ የከተማው ሰይጣን ጎታች ነውም፤ ተብያለሁ:: ግን፤ ጠንቋይና መተተኛ አይደለሁም::

እስከ ዛሬ ድረስ ብዙዎች ስለእኔ የፈለጉትን ብለዋል:: ኋሁንም እንደተለመደው የፈለጉትን ማለት ይችላሉ:: ማንም ምንም ቢል፤ እኔ ግን፤ ኃያሉ አምላካችን እግዚአብሔር የሰጠኝን መንፈሳዊ ጸጋ ጠብቄና ተጠቅሜ፤ የስብከትና የፈውስ አገልግሎት እየሰጠሁ የምገኝ መሆኑን፤ ከወዲሁ በአጽኖት ለማረጋገጥ እወዳለሁ::

እኔ አዳኝ አይደለሁም፤ ነኝ ብዬ ተናግሬም ሆነ ተመጻድቄ አላውቅም:: አገልግሎት እየሰጠሁ እንጂ፤ የሚፈውስና የሚያድነው እግዚአብሔር አምላክ ነው:: ዋንኛ ዓላማዬ፤ ለመንፈሳዊ ጥሪያችን እንቅፋት የሆኑትንና የሚሆኑትን መናፍስት በመለየት፤ ፈጣሪያችንን አክብረን በጸጋው ሙላት ውስጥ በመንፈሳዊ ብርሃን እንድናድግና ለሌላው ወገን በቀናነትና በበጎነት መትረፍ እንችል ዘንድ፤ ለሕሊናችንና ለልቦናችን የክፉ መንፈሶችን ድርጊትና የጥቃት ሥልቶቻቸውን በመጠቆም፤ ጠላቶቻችንን እንድንዋጋ ለማድረግ ነው:: ከዚህ ያለፈና የወጣ ድብቅ አጀንዳና ፍላጎት የለኝም:: ወገኖቼ ሁሉ ይህንን በጥሞና እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ::

አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼን ያገለገልኩ እየመሰለኝ የምከፍተው በር፤ የበለጠ የጎዳኝ ሆኖ ሳገኘው፤ ግራ ይገባኛል:: ተጨባጭነት የሌላቸውን መረጃዎች ተንተርሰው፤ አግባብ ባልሆነ መንገድ ሰብዕናን የሚነካ ነቀፋ፤ በተለይ ከማገለግላቸው ወገኖቼና ከእግዚአብሔር ቤት ሰዎች ሲሰነዘርብኝ፤ በጣም አዝናለሁ::

ስለሆነም በቤቱ ከምንመላለስ አገልጋዮች ጀምሮ እስከ ምዕመናን ድረስ፤ በተንኮለኝነት፣ በተቃዋሚነት፣ በተቺነትና በፌዘኝነት መንፈስ





ከመቆማችን በፊት፤ ቅድሚያ ሰጥተን መሥራት ያለብን፤ በክፉ መንፈሶች ገና በማለዳ ተይዞ የሚናውዘውን ተጠቂ ምስኪን ዜጋችንን ሥቃይና ስቆቃ ተረድተን፤ በዲያብሎስ የጽልመት ዓለም ውስጥ ታስሮ የሚገኘውን ጎስቋላ ወገናችንን ችግር ተገንዝበን፤ መታደግ የሚችል ሕሊናና ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲኖረን እንዲሁም፤ ሩህሩህ ልቦና እንዲሰጠን፤ በመጸለይ ነው::

ጥላቻ የተጣለው መልአክ፤ የሰይጣን ዲያብሎስ ምሪት ነው:: እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የሰጠንን ትክክለኛ የማገናዘብ ችሎታ ተጠቅመን፤ ከተቃውሞ በፊት፤ አገልግሎቱን ሥፍራው ላይ በአካል ተገኝቶ መገንዘብና ማስተዋል፤ የሚወደድ ትልቅ ጥበብ ይመስለኛል:: ተቃውሞው ከዚያ በኋላ ቢሆን፤ የሚመረጥና ሚዛናዊነቱን የጠበቀ እንዲሁም፤ ከጭፍን ጥላቻ የሚያላቅቀን ይሆናል::

የእግዚአብሔር የሆነውን መለየትና መረዳት ካልቻልን ግን፤ ተቃውሞችን መሠረተ-ቢስ ብቻ ሳይሆን፤ በዋናነት በታላቅ ቁጣ የወረደውን ዲያብሎስን የሚያግዝ ይሆናል::

እግዚአብሔር ያድናል! የእግዚአብሔር የሆነውን አንጠራጠር! አንቃወም! ዲያብሎስን ወደ እኛ የሚያቃርቡ መንገዶችን እንዋጋ እንጂ፤ እውነታውን እያወቅን፤ ለጠላታችን ጥቃት በር የምንከፍት ሰዎች መሆን አይኖርብንም::

ይህ ልመና ሳይሆን፤ መደረግ የሚገባው ነው:: በአጠቃላይ ቀጥተኛ መልዕክቴ፤ ጠላታችን የሆነው ዲያብሎስ እንደሚወጋን፤ እኛም፤ ነቅተንና ጠንክረን እንዋጋው! የሚል ነው::

**መጽሐፍ ቅዱስ በመዝ. 145(146) ፥6-9 ‹‹ እውነትን ለዘላለም የሚጠብቅ፤ ለተበደሉት የሚፈርድ፤ ለተራቡ ምግብን የሚሰጥ ነው:: እግዚአብሔር የታሰሩትን ይፈታል፤ እግዚአብሔር የወደቁትን ያነሣል፤ እግዚአብሔር ዕውሮችን ጥበበኞች ያደርጋቸዋል፤ እግዚአብሔር ጻድቃንን ይወድዳል፤ እግዚአብሔር ስደተኞችን**

ይጠብቃል፤ ድሃ አደጎችንና ባልቴቶችን ይቀበላል፤ የኃጢአተኞችንም መንገድ ያጠፋል። » ይላል።

እኛም፤ የኃያሉ አምላካችን የእግዚአብሔር ጥበቃና ምሕረት አብሮን እስካለ ድረስ፤ እንደተያዝን አንቀርም። ከታሰርንበት እንፈታለን፤ ከወደቅንበትም እንነሣለን!

**የእግዚአብሔር አምላክ ቸርነትና ሰላም፤ ከሁላችን ጋር ይሁን! አሜን!**

**መልካም ንባብ**

**መልአከ መንክራት ግርማ ወንድሙ**

**አዲስ አበባ መስከረም 2005 ዓ.ም.**

ለአስተያየትም፤
ፖ.ሣ. ቁ. 59286
አዲስ አበባ





## ምዕራፍ አንድ

## 1. የክፉ መንፈሶች ድርጊት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን።

**«የዘመኑንስ ምልክት መለየት አትችሉምን? » ማቴ.16÷3**

የክፉ መንፈስ ድርጊት ማለት፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፤ በሰው አማካይነት፤ ሌሎችን ለመጉዳት ተብሎ፤ ከአጋንንት ጋር የሚመሠረትና የሚደረግ ግንኙነት ማለት ነው።

ክፉ መንፈሶች በሕይወታችን፤ በኑሯችንና በዘመናችን ውስጥ ጣልቃ በመግባት፤ ጉዳት የሚያደርሱ አደገኞች ይሁኑ እንጂ፤ የእግዚአብሔር አምላክ ጥበቃ እስካለድረስ፤ የጥፋት አቅምና ኃይላቸው ፍጹም ውሱን የሚሆነው የእምነትና የአምልኮት ጥንካሬ ሲኖር ብቻ ነው።

ዛሬ የክፉ መናፍስቱ ጥቃት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የተስፋፋና የተመቻቸ፤ ጉዳት የማድረስ ችሎታቸው፤ የዚያኑ ያህል የተጠናከረ ከመሆኑም በላይ፤ የሕብረተሰብን ማህበራዊ አኗኗርን በመለማመድና በመመሳሰል የክፉ መንፈስ ጥቃት የረቀቀ ሥልታዊ ሆኖአል ።

ለእነዚህ የሰው ልጆች ጠላቶች ፍጹም መጠናከር፤ ከፍተኛ ርዳታና እገዛ ያደረጉት ደግሞ፤ በሚያስገርም ሁኔታ፤ ራሳቸው ሰዎች ናቸው።

**እንዴት?**

እስቲ ሁሉንም በዝርዝር እንመልከት።

**«እግዚአብሔር የሚወዱትን ሁሉ ይጠብቃል፤»**

**መዝ.144 (145)20**

## 1.1 <u>የዛር መንፈስ፤</u>

ዛር የሚለው ከዘር የተወረሰ፣ ከዘር የመጣ፣ በዘር የሚሄድ ማለት ሲሆን፤ ትርጉሙም፤ ለሰው ዘር ተመሳሳይ ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ያላቸው ሁሉ፤ በዘር ውስጥ ማለፋቸውን የሚያሳይ ምልክት ነው።

የዛር አጋንንትና ሰይጣን በቤተሰብ ውስጥ ሲመለክና ሲገበር ቆይቶ፤ ከአምላኪዎቹ የሚወለዱት ልጆች ሁሉ፤ መንፈሱ አብሯቸው ተወልደና አድጎ፤ መጨረሻ ላይ፤ የእኔ ዘር ናቸው በማለት በኃይል ያርፍባቸዋል።

በዚህ ረገድ <u>ዲያብሎስ ልዩ የሆኑ በአራት የተከፈሉ ዕቅዶች አሉት</u>።

- የሰውን ሕይወት ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠርና መምራት፤ የሚሔድበትን አቅጣጫ መለየት፤
- በከፍተኛ ፍጥነትና ግፊት ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረግ፤
- የጥቃት አድማሱን ማስፋፋትና መገምገም፤
- ለጊዜው በአጥቂነት የሚጠቀምባቸውን ሰዎች መሣሪያዎቹ በማድረግ፤ የኢኮኖሚ አቅም ማጎለበት፣ ክብርና ዝናን ማጎናጸፍ፤ ሌሎች ብዙዎች የሚጠፉበትን መንገድ ማመቻቸትና በተግባር መፈፀሙን ማረጋገጥ ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የሳጥናኤል እቅዶች ሲሆኑ በአፈጻጸሙ ሂደት ውስጥ ለሰብዓዊው ፍጡር መረጃ እንዲያገኝ ምንም አይነት ፍንጭ አይሰጥም።

የክፉ መንፈሶች የገሐዱ ዓለም ላይ በተጨባጭ ገጽታ አለመታየታቸው ብዙውን የሰው ልጅ የትውልድ ሐልውናን ሲፈታተኑ፤ ከመኖራቸውም በላይ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠውን ተስፋ ክብር ጸጋና በረከትና ሞገስን እንዳያገኝ ለመፋለም የራሳቸውን ክፋትና ጥፋት መፈጸሚያ በማድረግ ሲጠቀሙበት ኖረዋል። ይህንንም በቃየን ሕይወት ማየት ይቻላል።





መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን የዛር ምልክት ለመጀመሪያ ጊዜ የታየውና ለዘር መበላሸት ምክንያት የሆነው ሰው፤ ቃየን ነው። ቃየን ማለት፤ ከእብራይስጥ ቋንቋ ወደ አማርኛ ሲተረጎም፤ የጦር አበጋዝ ማለት ነው።

<u>የአቤልና የቃየን መስዋዕት በእግዚአብሔር ፊት፤</u>

‹‹እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም።›› ዘፍ. 4÷4-6 ቃየን እጅግ ተናደደ፤ ፊቱም ጠቆረ። እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፤ ‹‹ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ? መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅህ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው። አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።›› አለው።

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጸት፤ <u>ኃጢአት ታደባለች፤ ፈቃድዋ እና በእርሷ ንገሥባት</u> የሚሉት <u>ሶስት ቃላት</u> የሚያመለክቱት፤ <u>የሴት ፆታን</u> ነው።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፤ ቃየን <u>የሴት ዛር አጋንንት</u> በጥፋት መንገድ እርሱንና ትውልዱን ትመራ ዘንድ ነገሠችበት።

የቃየን መስዋዕት የስስት፣ የንፉግነትና እግዚአብሔርን የማይፈራና የማያመልክ መሆኑን ዲያብሎስ ስላወቀ፤ እርሱን ለክፋት፣ ለቅናት፣ ለንዴትና ለፊት ማጥቆር እርግማን በመሣሪያነት መግለጫው ፀማድረግ ምድራዊ የኃጢአት አሠራርና ሞት በይፋ መንገድ አገኘ። በዚህ የተነሳም፤ ንጹህ ወንድሙን አቤልን አለምንም በደል፤ በጥላቻና በልበ ቂመኝነት ተነሳስቶ፤ በድንጋይ ወግሮና ደሙን አፍስሶ ገድሎታል።

ስለዚህ የቃየን መንፈስ፤ የደም አፍሳሽነት ወይም የግድያ ወንጀል ጀማሪ በመሆን፤ ዲያብሎስን የሰው ልጅ ዘር አጥፊነትን በገሐዱ ዓለም ያለ እድሜ መሞትን ማሳያ በማድረግ ተጠቀመበት።

- እንሞክረው፣ እንየው፣ ለጥናት ጥሩ ነው በማለት፤ ጫት፣ አብሮም ሲጋራ፤ በመቀጠልም ሺሻ፣ ሐሺሽ፣ መጠጥ ወዘተ. ይጀምራል።
- ከአደንዛዥ ዕፆች በተጓዳኝ፤ የወሲብ ፊልሞችን በጋራና በተናጠል በመመልከት፤ የኃጢአት ንግሥቷ ዛር በውስጣቸው ቤቷን ትሠራለች፤
- የኃጥያቷን ንግሥት የሚያበረታቱ ዘፈኖች፤ ከወሲብ ቀስቃሽ አለባበስ ጋር በመታጀብ፤ ልቅ የሆነ ጠባይ እንዲወርሱ ያደርጋል።
- የሚያስፈሩና የሚያሰቅቁ (ሆረር) ፊልሞች ውስጥ፣ ደም የሚመጡ የሰው ፍጡሮችን፣ ቤት፣ መንገድ፣ ንብረት፣ በፈንጂና በሮኬት፣ በአውሮፕላን ድብደባ ሲወድም፣ የሰው ሕይወት በአሰቃቂ ሁኔታ ሲያልፍና አካሉ ሲጎድል በማሳየት፣ ዕድሉን ከፊልሙ ጋር እንዲያያዝ አድርገው፤ እያደር የወደፊቱ ዕጣ ፈንታው በመንፈሱ ወይም በመንፈስዋ እንዲወስን መንገድ ይጠርጋል።

  ከዚህ በኋላ ትውልዱ ጥፋትን አይቶና ተምሮ በመንፈሱ ተገዶ ክፋትን ቢሠራና ቢፈጽም፤ የሚያስቆጭና የሚያስገርም አይሆንም። ሌሎች ተመሳሳይ የጥፋት መንገዶችም እንደቀልድና እንደዋዛ፤ ከዘመናዊነት ውስጥ በመመንጨት፣ ትውልዱን ወደተበላሸ አቅጣጫ ሲወስዱት ብዙ ጊዜ ተስተውሏል። ይህ ሁሉ የመናፍስቱ ድርጊትና የጥቃት ሥልት መሆኑ በአንክሮ ሊታወቅ ይገባል።
- በኃጢአት ንግሥት ዛር የተለከፉ ሰዎች ሁሉ፤ ያዩትንና የሰሙትን፣ ያደረጉትንና የፈጸሙትን፣ ወደ ማዕረግና ወደ ሥልጣን በማውጣት፤ ከመልካም ነገር ይልቅ፤ ክፋትን





በማበረታታት፤ ክፉዋንና ክፉውን መንፈስ የሚጠቅሙ አገልጋዮቹ ይሆናሉ።

- በዚህ ክፍለ ዘመን ያለው ትውልድ፤ ከትምህርትና ከእውቀት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከሚገጥሙት ፈተናዎች መካከል፤ በኢንተርኔት ላይ <u>ያለ ሥራ ተጎልቶ በሚጨርሰው ሰፊ ጊዜ</u> የተነሳ፤ በዓይን ላይ በሚያርፉ የሱስ መንፈሶች በላቀ ሁኔታ እየተጠቃ የመገኘቱ ሁኔታ አንዱ ነው። እነዚህ በኢንተርኔት ማለትም በምስጢራዊ <u>የአጋንንት አምልኮት ሥር የሚለቀቁ</u> የመንፈሱ የአስተሳሰብና የክህደት ዘዴዎች፤ የሳይክሎጂ፣ የስሜት፣ የወሲብ፣ የአስትሮሎጂ፣ ወዘተ... ተዋጽኦዎችን በሙሉ የሚያጠቃልሉ ሲሆን፤ በምንስጣቸው ከፍተኛ አትኩሮትና ተመሥጦ የተነሳ፤ የሚገቡ መንፈሶች ናቸው። ብዙ ጊዜ በኢንተርኔት ላይ <u>ያለ ተጨባጭ ሥራ ተጎልተው የሚያሳልፉ</u> ሰዎች፤ ልክ እንደ ካርታ ሱስ ውለው ቢያድሩበት ሳይሰለቹም። አንዳንዶቹ ውለው እንዳደሩበት ምን እንዳዩ እንኳን ሲጠየቁ፤ አስታውሰው ለመናገር ያዳግታቸዋል።
- በዚህ የኢንተርኔት ሱስ የተለከፉ <u>ሰዎች፤ በሳይንሳዊ ትንታኔ ሕብረተሰቡንና ቤተሰባቸውን ግራ በማጋባትና በማስቸገር፤ ሌሎችን ከእምነት ጎዳናና አምባ ለማሰወጣት</u>፤ በንቀት ቋንቋ የሚናገሩ፣ የሚተቹ፣ የሚቃወሙ፣ የሚያፌዙና አዋቂዎች ሆነው ለመቅረብ የሚጥሩ፤ በአጠቃላይ፤ ክፉው መንፈስ የሚመላለስባቸው ማደሪያው ይሆናሉ።

  ይህ የሚያመለክተን፤ <u>ክፉ መንፈሶች የዘመኑን የእውቀትና የቴክኒዎሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም</u>፤ በረቀቀ ጥበብ፣ ከእግዚአብሔር መንገድ እንዴት እንደሚያርቁ፣ የሞትና

የነፍስ ጉዳት በማድረስ ላይ የሚገኙ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ይህ ማለት ግን፤ ኢንተርኔትን ጨምሮ ሌሎች የቴክኒዎሎጂ ውጤቶች በሙሉ፤ ለዲያብሎስ የቆሙ የመንፈሱ መሣሪያዎች ናቸው፤ <u>ማለት ሳይሆን</u>፤ በዚህ ረገድ ኃጢአትን የሚያበረታታውን፣ ነውርና ከሞራል ሥነ-ምግባር የወጣውን፣ በአጠቃላይ ክፉ መንፈስ የሚመራውንና <u>ከእግዚአብሔር ሕግ የወጣውን</u>፤ በተለይ በኢንተርኔት የሚለቀቁትን <u>የክፉውን መንፈስ መልዕክቶችን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማመልከት</u> ነው።

በአጭሩ፤ ኢንተርኔት የሚጠቅመንን ያህል፤ በዚህ መንገድ ከተጠቀምንበት ደግሞ፤ሊጎዳን እንደሚችል የሚጠረጥር መሆን የለበትም። የሚፈውስ መድኃኒት እንዳለ ሁሉ፤ የሚገድልም መድኃኒት አለ። ብርሃን እንዳለ ሁሉ፤ ጨለማም አለና!።

እንዲህ ዓይነት ችግሮችን <u>በዘመናዊው መንፈስ ተጽዕኖ ያዳበሩ</u> ሰዎች ባሉበት አካባቢና መንደር የሚወለዱ ልጆች፤ ወላጆቻቸውን ጨምሮ፤ ጭንቀት፣ መረበሽ፣ የልብ መደንገጥ፣ እንቅልፍ ማጣትና መቃተት፣ ጠብና ሳያውቁት መነጫነጭ፣ መበሳጨትና ግልፍተኛ መሆን፣ ዕቃ መስበር፣ መግዛትና ደግሞ መስበር፣ በድርጊቱም መርካት፤ የባልና ሚስት መለያየት መበጣበጥና መጯጯኽ፤ ሌሊት ሳያውቁት በር ከፍቶ መውጣት፣ ገንዘብን ከቦርሳ አውጥቶ መጣል፣ ቀን መደበትና ሌሊት መንቃት፣ ሞትን መፈለግና በተቃራኒው ማማረር ወዘተ… መንፈሱና ሰዎቹ ያሉበት አካባቢ መለያ ባሕርይ ነው።





<u>በአካባቢው የሚወለዱ ልጆች ጠባይ</u>

በአብዛኛው ቅብጥብጥ፣ ትምህርት የማይወዱ፣ የአመጋገብ ፍላጎታቸው የተዘበራረቀ፣ አንድ ጊዜ ከአቅም በላይ የሚበሉ ሲሆን፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ምንም የማይቀምሱ፣ ስማቸውንም ቤተሰባቸውንም የሚረሱ፣ ደንታ የሌላቸው፣ መፍዘዝና ግራ መጋባት የሚታይባቸው፤ እንዲሁም እሺን የማያውቁ ሁልጊዜ የአፍ መፍቻቸው እንቢ ወይም ኖ (No) ብቻን የሚናገሩ፣ የማይታዘዙ፣ የማይደፈረውን የሚደፍሩና የማይናቀውን የሚንቁ፣ በአንፃሩ ደግሞ፤ የሚናቀውና የሚደፈረው የሚከብዳቸው፤ ተቃራኒ ጠባዮች የሚስተዋልባቸው ይሆናሉ።

ፊልም ማየት የሚወዱ፤ ለብቻቸው በሕልም መንፈሱ ወሲብን ሲያስተምራቸው የሚያዩ፤ ገለልተኛና ብቸኝነት የሚመቻቸው ሆነው፤ ከነበረው ትውልድ ወጣ በማለት በአካልና በአስተሳሰብ የተለዩ ሆነው ይወለዳሉ።

<u>ቃየንና የቃየን ቤተሰብ ውጤት</u>

የቃየኒ ንፉግና በረከተ-ቢስ፣ ፍቅር አልባና፣ የአስተሳሰብ ክፉነት ለራሱና ለትውልዱ ብዙ መዘዞችን አስከትሏል።

- ቡቃየን ሕይወት ውስጥ ትልቁ ችግር የፍቅር መንፈስ ሚጣትና አለመገለጥ ነው። ለጠብና ለተንኮል፣ ግፍና ለግድያ ወዘተ… ለመሳሰሉት የወንጀል ጀማሪዎች መከሰቻ ሆኖአል።
- ፍቅር መልክ የሚይዘውና ውበት የሚያገኘው ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ንጹህ አምልኮት ጋር ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ እውነት ከወጣ ግን ፍቅር ሚዛኑንና አቅጣጫውን በመሳት፤ የመዘበራረቅ ዕድሉ እጅግ የሰፋ ነው። በቃየን ሕይወት ውስጥ የታየው ፍቅር፤ የጦርነት፣ የዘፋኝነትና ከቦታ ቦታ የመንከራተት፣ የወንዝ ውኃ መንፈስ የተጀመረበት፣ የባዕድ

አምልኮትና የኃይል ኑሮ ትውልድ የበቀል ሞት አስተማሪ በመሆን የእሳቹን መንፈስ አገልግለዋል፡፡

- በዚህም፤ አስተሳሰብ፤ ገሐዳዊውን ዓለምና የባለ አስተሳሰቡን ሕይወት፣ ኑሮና ትውልድ የሚወስን እንደሚሆን ከቃየን መገንዘብ እንደሚቻል ግልጽ ነው፡፡ ቃየን በወንድሙ ላይ በጥላቻ በመነሳት የውስጥ አስተሳሰብ ሂደት ያመጣው ውጤት፤ ወደ ክፉ አምርቶ፤ ሽፍትነትን፣ ውንብድናን፣ ስደተኛነትን፣ ኮብላይነትንና ክዳትን እንዲሁም፤ ከእግዚአብሔር እምነትና አምልኮት የራቀ ትውልድ ጠባይ እንዲሆን ዓይነተኛ ገጽታ ሆኖ እየኖረ ነው፡፡ ለክፉ ተግባር በመነሳሳት ግፊት ውስጥ ክፉው መንፈስ በአዳም ልጅ በቃየን ላይ ዕድል በማግኘቱ፤ ጥፋትን ለመግለጥ ተጨማሪ መነሻ መንገድ እንዲያገኝ ረድቶታል፡፡

## የቃየን ገጸ ባሕርይ ለክፉው ዓለም

ዛሬ በዓለም ላይ ካለው የንፉግነት የውስጥ አስተሳሰብ በብዛት ተከስቶ የሚታየው በእግዚአብሔር ስም የሚደርጉ ክንውኖች ናቸው፡፡ እነዚህም በጎነት ማጣትና የእምነት ዋጋን ከነ ጭራሹ በመተው፤ በመርሳትና በመዘንጋት መካከል በሕልውና ውስጥ የበረከት ጅማሬ በአምላክ እንዳይመጣ ማገጃ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ፤ የኑሮ ተስፋና የትውልድ ሰማያዊ ሥጦታ ላይ ሁለንተናዊ እጦትን እንዳመጣ በቃየን ሕይወት መማር ይቻላል፡፡

ቃየን ለእግዚአብሔር የአምልኮና የክብር መስዋዕት ለመስጠት ፈቃድኛ ያልሆነ፤ የመጀመሪያው ንፉግ ሰው በመሆን፤ የጉልበቱ ዋጋ በእምነት መስዋዕት በኩል አልተገለጠም፡፡ ስለዚህ ቃየን በየትኛውም ትውልድ ላሉ ንፉግ ሰዎች ምሳሌ በማድረግ፤ ዲያብሎስ የመቅኖ-ቢስነትን አኗኗር በዓለም ላይ ገልጦበታል፡፡





የበረከትን ጣዕም አለማወቅ በሰው ልጅ ዘር ውስጥ አንድ ብሎ የጀመረው በቃየን ሕይወት ውስጥ ነው፡፡ ቃየንና ዘሩ ዕድሜያቸው ያለቀው በረከትን ለማግኘት በራሳቸው ዘዴና ጥበብ ሲፈልጉ፤ በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ በመሆን፤ ዕድሜ ልካቸውን የጦርነት የዳንኪራና የወንዝ አምልኮት ባሕልን ያዳበሩ በመሆናቸው፤ በቃየን ትውልድ ውስጥ ክፉው መንፈስ እነርሱን በመያዝ፤ የሕብረተሰብ አካል የመሆን ዕድል አግኝተዋል፡፡

በእግዚአብሔር ያልተጠበቀ በረከት፣ ፍላጎትና ተግባር፣ ያልተቀደሰ ትውልድ ምልክቱም እንደ ቃየን በመንፈሳዊ ሕይወት መቅበዝበዝ መሆኑን ለዓለም ምልክት የጥፋት አርዓያ ሆኖአል፡፡

## የካደው ትውልድ ቋንቋ፤

‹‹አላውቀውም፤ የወንድሜ ጠባቂ እኔ ነኝን?›› የሚለው የቀደመው ቋንቋ በዚህ ዘመንም ይንጸባረቃል፡፡ ፆም ጸሎት አላውቅም፤ የአባቶቻችንን መንፈሳዊውና ሥጋዊ ታሪካቸውን እንዲሁም ተጋድሎአቸውን አላውቅም፤ እኔ የእነሱ ጠበቂ ነኝን? የሚለው የቃየን ቃል፤ ዛሬም ይሠራል፡፡

ይህ ያዛር እልህ፣ የደም እርግማን፣ የወንጀል ጩኸት፤ የአሁኑ ዘመናችንን እያሳየና በግልጽ እየመሰከረ ነው፡፡ ጸድቃንና ቅዱሳንን አላውቅም የሚለው የመናፍቁ መንፈስ አንዱና ዋናው የዚህ የካደው ትውልድ ቋንቋና መግለጫ ነው፡፡

ምክንያቶች ሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወራቸው የተነሣ፤ በሰሜን ያለው መንፈስ፤ በደቡብ፣ በምዕራብ ያለው፤ በሰሜን፣ በመሐል ያለው መንፈስ በምስራቅ ወዘተ… ሊኖር ይችላል።

## <u>የዛር መንፈሶች ለሰዎች የሚያወርሱዋቸው አጠቃላይ ጠባያት፤</u>

በየሰዓቱ የሚቀያየር ጠባይና የተደበቀ ስውር ሰው መሆን፤ ውስጥ ውስጡን መሸመቅ፤ እልኸኝነት፣ ወይም ከሚገባው በላይ ግልጽ መሆን፤ ብዙን ጊዜ በንዴት በብስጭት ጊዜውን ማሳለፍ፣ በር ዘግቶ በጨለማ መቀመጥ፣ ለብቻ ማልቀስ፣ ወሬ ማናፈስ፣ ነገር ከያዘ አለመልቀቅ፣ የዓመል ግትርነት፣ የእግዚአብሔርን ሰው መጥላት፣ ማሳደድ፣ ደምን ማፍሰስ፣ ደም ሲፈስ ማየት፣ ተበቃይ፣ ቂመኛ፤ አመጸኝነት፣ መጋደል፣ ሌላውን በክፉ ዓይን ማየት፣ በተለይም በሌላው ኑሮና አምልኮት፣ በእግዚአብሔር ጸጋና ሞገስ መቅናት፣ በሌላው ዕድገት ፊትን ማጥቆር፣ ስም ማጥፋት፣ መተቸት፣ መቃወም፣ ማፌዝ፣ መሳደብ፣ መራገም፣ ሐሜት፤ አሽሙር፣ መራራ ቃል መናገርና እንደሱስ መሆን፣ በገንዘብ፣ በሥልጣንና በጉልበት መሣሪያነት መተናከል፣ ለሌላው ውድቀትና ሞት መመኘት፣ ለማጥፋትና ለማውደም መቸኮል፣ የሌሎችን ኪሳራና ውድቀት በማየት መደሰት፣ ሃይማኖት መለዋወጥና የእምነት አለመኖር፤ ወዘተ… የመሳሰሉት ሁሉ፤ ዛር ያለባቸው ሰዎች የተለመዱ ጠባያት ናቸው።

የዛር መንፈሶች <u>በአብዛኛው ተመሣሣይ ጉዳት</u> የሚያደርሱ ቢሆንም፤ በዋነኛነት ግን፤ ከማሕፀን ጀምሮ ልክፍት የሚሆኑ፣ የሰው ልጆችን፤ ከርታታ፣ ባካኝ፣ ሠርቶ መና የሚያደርጉና የመከራ ኑሮን የሚያወርሱ ናቸው።





የዛርና የውቃቢ የውርስ መንፈሶች፤ ሌሎች ወደ ሰዎች የሚላኩ የዲያብሎስ መንፈሶችን፤ በመሳብና በፍጥነት ተቀብሎ ቦታ ሰጥቶ በማስተናገድ፤ በውስጣችን ሰይጣንን አሰባስቦ በማደራጀት ሰፊ ጠባያቸውም፤ ይታወቃሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱን አዳኝ ወርቄ የተባለውን መንፈስ፤ <u>በምሣሌነት</u> እንመልከት።

## <u>አዳኝ ወርቄ</u>፤

መልካም መዓዛ ያለው ሽቶና እጣን፤ ከጌጣጌጥ ወርቅ በብዛት የሚወድ ሲሆን፤ መልክና ውበት ያላትን ሴት ከሌላ ወንድ አስቀድሞ ለራሱ እንደሚስት ስለሚይዝ፤ የዚህ መንፈስ ሰለባ የሆኑ ብዙ ሴቶች ባል አያገቡም፤ አይፈልጉም።

ስለዚህ የባል ፍቅርን ሳያዩ፣ ልጅም ሳያምራቸው፤ የቤተሰብ ኃላፊነትም ሳይሰማቸው ቀርቶ፤ <u>ዘመናቸውን ከመንፈሱ ጋር ይጨርሳሉ</u>። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፤ ልጅ <u>የመውለጃ ዕድሜያቸው ካለፈ በኋላ በተቃራኒው</u>፤ መንፈሱ በውስጣቸው ልጅ መውለድ እንዲያምራቸውና፤ እንዲጓጉ በማድረግ፤ የቁጭት ስሜት ያሳድርባቸዋል። በዚህም የተነሣ፤ ውስጥ ውስጡን እየተብከነከኑና፤ በመካንነታቸው እያዘኑ፤ ፈጣሪ አምላካቸውን እያማረሩ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል። የክፉው መንፈስ ዋንኛ ዓላማ፤ ሰዎች በሕይወታቸው እግዚአብሔርን እንዲያማርሩ ስለሆነ፤ በዚህ በኩል የሚያደርገው እንቅስቃሴ የተቃና ይሆንለታል።

የአዳኝ ወርቄ ዛር ጠባይ፤ ሴት ልጁን ያኳኩላል፣ ወርቅ በጸጉርዋ፣ በአንገትዋና በጆሮዋ፣ በእግርዋና በእጅዋ ላይ ያበዛል። ራሱም ልዩ ውበት የመስጠት ኃይል ያለው ሲሆን፤ በገሃዱ ዓለም ያለ ሌላ ወንድ ሲጠጋት ወይም ሲያያት ይማረክባታል፤ የሩካቤ ፍላጎትንም እንዲሰማው ያደርጋል። ይሁን እንጂ፤ በአብዛኛው ሴቲቱ ከወንድ ጋር ለመሆን አትፈልግም።

መንፈሱ ከብዙ ወንዶች ጋር የሚያገናኛት ቢሆንም፤ ከሁሉም ጋር አያግባባትም። ምክንያቱም፤ ደም ስለሚፈልግ፤ ከሁለቱ አንዱን ወይም ሁለቱንም ለማጋጨት ብሎም ለማጋደል ስለሚፈልግ ነው።

ባለጸጋዎችን፣ ሹፌሮችን እና ነጋዴዎችን ወዘተ.... በመጥለፍ ገንዘባቸውን ይሰልባቸዋል። ልባቸው ላይ መልኳንና ውበቷን ያስቀምጣል። እስኪያገኟትም ድረስ፤ እንቅልፍ ይከለክላቸዋል፤ ይረብሻቸዋል። አንዳንዶቹ እስኪያብዱ ድረስ ይፈትናቸዋል።

ይህ እንግዲህ መንፈሱ ሴቲቱን በሃብት ለማበልፀግ የሚሄድበት መንገድና ለኃጢአት አሠራሩ የሚጠቀምበት ዘዴ ነው።

እንዲህ ዓይነቷ ሴት አንዱን ቀን፤ ለተማረከባት፣ ሀብቱን ላፈሰሰባት ወንድ ስትሰጥ፤ ሁለት ወይም ሶስት ቀን ደግሞ የመንፈሱ ተራ ይሆናል። ይህ፤ ከመንፈሱ ጋር የምትገናኝበት ጊዜ መሆኑ ነው።

በዚህ ወቅት ዕጣን፣ ሉባንጃ፣ ሽቶ የመንፈሱ አልባሳት ሁሉ ሳይቀር ይዘጋጃል። የሚጠይቃቸው የግብር ዓይነቶች ሁሉ ከተሟላ በኋላ፤ በነጋታው ገንዘብ የሚያፈስላትን ሰው ያዘጋጅላታል። የሰውየውን አቋም፣ ተክለ-ሰውነት፤ መልክና ውበቱን፤ በሕልሙዋ አስቀድሞ ሊጠቁማትም ይችላል።

ሌላው ጠባዩ፤ ዓይን ለዓይን በመተያየት፣ በድምጽ (በስልክ ውስጥ የሚደረግ ንግግርን ይጨምራል)፣ ሰላምታ በመጨባበጥ፤ በልብስ በመነካካት ወዘተ... ሁሉ ሳይቀር፤ የፍትወት ስሜትን ያነሣሣል።

በአብዛኛው ከተለመደው የተፈጥሮ ባሕርይ ወጣ ያለ የወሲብ ስሜትን የሚፈጥረው <u>ክፉ መንፈስ</u> መሆኑን ብዙዎች አይገነዘቡትም።





<u>ለምሳሌ</u>፤ አስገድዶ የመድፈር ጠባይ፤ የዚህ የዝሙት መንፈስ አንዱ አካልና መገለጫ ነው።

## <u>ለመለያየት የሚጠቀምበት ዘዴ</u>

ከጊዜ በኋላ ሴቲቷን የተጠጋውን ሰው፤ የማያቋርጥ ከባድ ራስምታት፤ ሆድ መንፋት፣ መደበት፣ ማስጨነቅ፣ በመሳሰሉት አስቸጋሪ ጠባያት፤ አማሮ ሊያባርረው ይችላል።

የተለያየ አካላዊ አደጋም ያበዛበታል። ጠቋርን የመሰለ ዛር ከሆነ ደግሞ፤ ከቅናቱ የተነሣ፤ ሕይወቱን ሊያጠፋው ሁሉ ይችላል። ሌላው በመንፈሱ የመገለጫ ጊዜ፤ ለእርስዋ በመኝታ ላይ ልታየውና ልትዳስሰው እንዲሁም፤ ሌሊት ክንድዋ ላይም ልታገኘው ትችላለች።

በዚህ መንገድ ብዙ ሴቶች የመንፈሱን ሩካቤ ያፈቅራሉ። ከባል ጋር ግንኙነት ባያደርጉ ፈቃዳቸው ነው። በተለያየ ምክንያት ግንኙነት ቢፈጽሙ እንኳን እርካታ አይኖራቸውም። በዚህ ግንኙነት የሚፈጠሩት ልጆች ደግሞ፤ በተፈጥሮና በአስተሳሰብ የተጎዱ ሆነው ይወለዳሉ። ከዚህ በተጨማሪም፤ የቡዳ መንፈስ አስተላላፊዎች በመሆን፤ ያሌሎችን ሕይወት ይጎዳሉ።

ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ፤ ከተኙበት ሲነቁ ግን፤ አቅፈው የተኙትን መንፈስ ገጽታ፤ በዓይነ-ሕሊናቸው ሲያስታውሱት፤ ከባድ መንፈሳዊ ቀውስ ውስጥ በመግባት፤ ከፍተኛ የሆነ ፍርሃትና ጭንቀት እንዲሁም ሽብር ውስጥ ይገባሉ፤ ይወድቃሉ።

በተለይ ይህንን ሁኔታና ሥቃያቸውን ለሌላው ሰው ለመንገር ስለሚያሣፍራቸው፤ ውስጣቸው እንደቆሰለ ይኖራሉ። « **ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ፤ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?** » **ማቴ. 16÷26**

## ሾተላይ የዛር የመተናኮል የውርጃ መንፈስ፤

ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ዛር ሾተላይ በመሆን፤ እርግዝና ላይ አደጋ የመፍጠር ችሎታ የሚኖረው ሲሆን፤ ተተኪ ትውልድን በማጨናገፍ የሚረካ፤ የሰው ደም በማፍሰስ የሚደሰት፣ና የቤተሰብን ሐዘንና ለቅሶን፤ በልጅ ማጣት መቸገራቸውን እያየ እንደ ድል የሚቆጥር፤ ስውር እልኸኛ የዛር መንፈስ ነው።

## የዛር መንፈስ ከማሕጸን ጀምሮ ያለው፤ ሌላው ጥቃት፤

ከማሕጸን የሚወረሱ የዛር መንፈሶች፤ የእናትና የአባት የመንፈስ ጉዳቶች ድምር ውጤት በመሆናቸው፤ ልጆቹ ሲወለዱ አብሮ በመወለድ፤ የሕጻናቱን ትክክለኛ የአካልና የአእምሮ ተፈጥሮን በማዛባት፤ የሚከተሉትን ጉዳቶች በዋናነት ያስከትላሉ።

ሀ. መካን (መኻን) ማድረግ፤

ለ. በሚወለዱ ሕጻናት ላይ፤የአእምሮ፣ የጤና እንከንና የአካል ጉዳት መፍጠር፤ ለምሣሌ፤- የዛር መንፈስ፤ አንዳንድ ሕፃናትን የአካል ጉዳተኛ፣ የአእምሮ ዘገምተኛ ወዘተ… ከማድረጉ በተቃራኒው፤ ያለዕድሜ ደረጃቸው እንዲያስቡና ሥራቸው ሁሉ፤ እንደ ትልቅ ሰው እንዲሆን ያደርጋል።

ብዙ ጊዜ እንደነዚህ ዓይነት ሕፃናት፤ አስተሳሰባቸው፤ ዕድሜያቸው ከሚሸከመው በላይ ስለሚሆን፤ ረዥም ዓመት በሕይወት የመቆየት ዕድላቸው የመነመነ ነው።

ሐ. የሚወለዱትን ልጆች ባሕርይ ማበላሸትና መጥፎ ጠባይን ማውረስ፤

መ. ያለዕድሜ፤ ተፈጥሯዊውን የወር አበባ ዑደትን ማዛባት፤

- ማለትም፤ሴት ሕጻናት ገና ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱና ጡት ሳያወጡ፤ በስምንትና በዘጠኝ ዓመት ዕድሜያቸው በሚያስደነግጥ ሁኔታ የወር አበባ እንዲያዩ ያደርጋል፤





- ሴት እህቶች ደግሞ፤ ባልተለመደና በማይጠበቅ ሁኔታ፤ በአብዛኛው በሰላሣና በሰላሣ አምስት ዓመት፤ እንዲሁም እስከ አርባ ዓመት ዕድሜ ክልል ላይ ሲደርሱ፤ የወር አበባ ማየት እንዲያቆሙና ያለጊዜያቸው እንዲያረጡ ያደርጋል።
- አንዳንዶቹም በዚሁ መንፈስ ጥቃት የተነሳ፤ ከሃያ ዓመት ዕድሜያቸው ጀምሮ፤ ለአንድ ወይም ለሁለት ዓመት፤ ወይም ከዚያም በላይ ለሚሆን ጊዜ፤ የወር አበባቸውን ሊያጠፋው ወይም ሳያዩ እንዲቆዩ ሊያደርግም ይችላል። ከዚህም በተቃራኒ፤ በአንድ ወር ውስጥ በተደጋጋሚ የወር አበባ እንዲፈሳቸው ያደርጋል።

በሕክምናው በኩል ሐኪሞች እንደሚገልጹት፤ « እንደዚህ ዓይነት ክስተቶች አዲስ አይደሉም። በተለያየ ምክንያት አልፎ አልፎ ሊፈጠሩ ይችላሉ። ሆኖም፤ በብዙ ሴቶች ላይ የመታየቱ ጉዳይ ግን፤ ያልተለመደና ራሱን የቻለ ጥናት የሚያስፈልገው ነው።» ይላሉ።

ነገር ግን፤ በርካታ ሰዎች ከላይ የተገለጹት ችግሮችና እንከኖች፤ በአንድ በኩል በዲያብሎስ ምሪት በክፉ መንፈሶች ተጽዕኖም ሊመጣ እንደሚችል፤ ገና መረጃው የላቸውም። በተደጋጋሚ እንደተገለጠው፤ ዲያብሎስ በዛር መንፈሶች በኩል ከሰዎች ጋር አብሮ እየተወለደና እየተወራረሰ፤ ዘሬ አድርጌያቸዋለሁ እያለና መንፈሱን ከማሕጸን ጀምሮ እያስቀመጠ፤ ክፍ ብሎ የተጠቀሱትን ጉዳቶች የሚያደርስ ቢሆንም፤ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚሸነፍና ወደ ሲኦል ወርዶ የሚታሰር ጠላት መሆኑን ለአፍታም ያህል፤ መጠራጠር የለብንም።

ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማርቆስ ወንጌል 9፥29 «ይህ ወገን በጸሎትና በጦም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም» ይላል። ይህ ማለት ወገን ሆኖ አብሮት ስለተወለደ በአካላዊ ተፈጥሮው ላይ ደንቆሮና ዲዳ በማድረግ የእናትና የአባቱ ሕልውና እንደጎዳ መመልከት ይቻላል።

## <u>ሴት ዛር በወንድ ላይ ስትኖር፤</u>
## <u>የምታመጣው ጉዳት</u>

ሴት ዛር ወንድን በምትይዝበትና አብራ ተወልዳ በምታድግበት ወቅት፤ ሕይወቱን ትለማመድና ልክ እንደሴት ልጅ በመቀመጫው በኩል በየወሩ የወር አበባ እንዲመጣበት ታደርጋለች።

ይህ ፈጽሞ ያልተለመደ ሁኔታ በሕክምናው በኩል፤ የአንጀት ጉዳት ወይም የኪንታሮት ችግር መስሎ እንዲታይ፤ መንፈሱ ማሳሳቻውን ያቀርባል። ምንም ይባል ምን፤ የሚገርመው ግን፤ በሰውየው ላይ የወር አበባ ዑደቱ ልክ እንደ ሴቶች ቀን እየጠበቀ ለዓመታት ያህል ያለማቋረጥ የመታየቱ ጉዳይ ነው።

ይህ የተዛባ ተፈጥሮ፤ የዛር መንፈስን የሚያመልኩና የሚገብሩ ሰዎች የበዙበት አካባቢ በሚገኙ ቤተሰቦችና ማሕበረሰብ ውስጥ በስፋት የሚገጥም ክስተት ነው።

## <u>ዝብረቃ</u>

በማይጠበቅ ሁኔታ ድንገት አስደንጋጭ የሆነ ቃል፤ በንግግር መሐል ላይ ዝብርቅ ማድረግ የተለመደ የዘመናችን ስልጡን ሕብረተሰብ ዋና ችግር ነው። ይህ፤ የዛር መንፈስ ሌላው ጥቃት ነው። ዝብረቃ <u>በሁለት</u> መልኩ ይከሰታል።

### ሀ. <u>የተሰወረ ዝብረቃ፤</u>

የመንፈሱ ምስጢራዊ አሠራር በሥራ፣ በትምህርት፣ በንግድ ሥራና ሙያ በዕቅድና በፖሊሲ ንድፈ ሐሳብ እንዲሁም በጸሎት ጊዜ ሁሉ ጣልቃ በመግባት፤ አደገኛ ነገርን የሚያመጣ የመሪዎችና የኃላፊዎች የዝብረቃ ትዕዛዝን ጨምሮ የዓለማችን ትልቁ በሕይወታችን ውስጥ የሚገኙ የመንፈስ ውጥረት ነው።





ለምሳሌ ዘብረቅ ያለ ዳኛም ይሁን መሪ ቶሎ ከእስር ቤት ሃምሳ ሰዎች ይረሸኑ ብሎ ከተናገረ፤ ሰውየው ሳያውቀው በዝብረቃ መንፈስ ሃምሳ ሰዎች ተገደሉ ማለት ነው።

በሕክምናውም በመድኃኒት ምርምሩም በተለያየ ኃላፊነትና የሥልጣንና የማዕረግ እርከን ያሉ ሰዎች ላይ የጦር መሪዎችንም ጨምሮ እስካልተወሰነ ሰዓት ድረስ፤ የዝብረቃ መንፈስ ያጠቃቸዋል።

### ለ. <u>ግልጽ ዝብረቃ፤</u>

ከፍሬ ነገሩ ጋር የማይገናኝና የማይያያዝ ሐሳብ ማስገባት፣ በጨዋታ መካከል ከመልካም ሥነ-ምግባር የወጣና የወረደ ቋንቋ መጠቀም፣ መሳደብ፣ ማዋረድ፣ ወይም ማልቀስ፤ በተቃራኒው፤ ከልክ በላይ መሳቅ፣ በሙሉ ሰውነት ድንገት ብድግ ብሎ መዝለልና ወድያውኑ የመቃተት ድምጽ ማሰማት፣ በእጅና በከንፈር ለብቻ ማውራት፣ ቁጭ ብሎ መዋተት፣ ሰዎችን ያለ ስማቸው አጠገባቸው ባለ ሰው ስም መጥራት፣ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን አለስማቸው መጥራት፤ ለምሳሌ፤ እንጀራ ለማለት፤ በቆሎ፣ ውኃ ለማለት፤ እንጨቱን አምጣና አንጠጣ ወዘተ ... ሁሉ ማለት፤ የዚህ ክፉ መንፈስ የሚታይና የሚሰማ የዝብረቃ አካል ነው።

## <u>ያለ ዕድሜ መጃጀት</u>

የዛር መንፈስ ከሚያስከትለው ጉዳቶች መካከል ፤ <u>ያለ ዕድሜ መጃጀት፣ መርሳትና መዘንጋት</u> አንዱ ነው። ይህ፤ በተለይ በአሁኑ ዘመን ትልቅ ችግር ሲሆን፤ ጥቃቱን በብዛት የሚያሳርፍባቸው፤ ሳይንቲስቶች፣ ፖለቲከኞች፣ ምሁራኖችና በኃላፊነት ሥልጣንና ማዕረግ የሚገኙ ሰዎች፤ ሴቶችን ጭምር መርሳትና መዘንጋት ከክፉው መንፈስ አንዱ መሠረታዊ ችግር ነው።

በሕክምናው (ዲያሜንሽያ) ብለው ስም ስለሰጡት፣ <u>በሳይንሳዊ ስያሜው መንፈስነቱን መደበቂያ ምሽግ</u> አድርጎታል።

ለጸሎት፣ ለአምልኮትና ለእግዚአብሔር ቃል ጊዜና ቦታ <u>የሌላቸው ሁሉ</u>፤ በዚህ ክፉ መንፈስ ይጠቃሉ።

<u>*መሠረታዊ ምልክቶቹ፤*</u>

- ያወጡትን ዕቅድና ፕሮግራም መርሳት፣ ወይም መተው፤
- ከሕሊናቸው፤ ዕውቀታቸውና ልምዳቸው መጥፋት ወይም መሰወር፤
- ገንዘባቸውንና ንብረታቸውን አለመቆጣጠር፤
- ከቤታቸው ወጥተው፤ የሚኖሩበት መንደር፣ መንገድና መኖሪያ ቤታቸው ጠፍቶአቸው ሌላውን ሰው እስከ መጠየቅ መድረስ፤
- ምሳ ወይም እራት በልተው፤ አልበላሁም ብለው መጣላት፣ ማኩረፍ፣ መናደድና መጮኽ፤
- ሚስታቸውንና ልጆቻቸውን መርሳት፤ አለ ዕድሜ በዚህ መንፈስ የመጠቃት ልዩ ምልክቶች ናቸው።

<u>አዋቂው ሰው እንደ ሕጻን መሆን</u>፤

ከዚህ በተቃራኒው፤ የዛር መንፈስ በዕድሜ ከፍ ያሉና የገፉ ሰዎችን፤ እንደ ሕጻን እንዲያስቡና እንዲሠሩ በማድረግ፤ መካሪና አስታራቂ በመሆኛ ዕድሜያቸው፣ እንዲሁም ባሪና ቀባሪ በሚያስፈልጋቸው ሰዓት፤ እንደ ልጅ አድርጎ ቅሌትና ውርደት ውስጥ ይከታቸዋል።





<u>ሾፌሮችንና ተሣፋሪዎችን በመንገዳቸው ላይ የሚያጠቁ ክፉ መንፈሶች፤</u>

ሰዎች በልዩ ልዩ ምክንያቶች በተለያዩ የትራንስፖርት ዘዴዎች ማለትም በአውሮፕላን፣ በመርከብ፣ በባቡርና በመኪና በመጠቀም፤ ከቦታ ወደ ቦታ ይዘዋወራሉ። ጉዞ ጀምረው በሚገጥማቸው አደጋ፤ ያሰቡበት ሥፍራ ሳይደርሱ ወጥተው የቀሩ፤ ወደ ቤታቸውና ወደ ቤተሰባቸው ያልተመለሱ ብዙዎች ናቸው።

በመጓጓዣ ዘዴዎች ላይ የሚደርሱ የመጋጨት፣ የመከስከስ፣ የመገልበጥ፣ የመቃጠል፣ የመስመጥ ወዘተ... አደጋዎች፤ ከግማሽ በላይ መንስኤያቸው <u>ከክፉ መናፍስት ምሪት ጋር የተያያዙ</u> ናቸው።

አውሮፕላን አብራሪዎች፣ የመርከብ ካፒቴኖች የባቡርና የመኪና ሾፌሮች፤ ኃላፊነታቸው የመክበዱን ያህል፤ የማይጸልዩና መንፈሱን በጸሎት አሥረው የማይንቀሳቀሱ ከሆነ፤ የመናፍስቱ ጥቃቶች የማያቋርጥ የመንገድ ላይ ጦርነት ይሆኑባቸዋል።

ብዙ ጊዜ በዲያብሎስ አማካኝነት በሁሉም የመጓጓዣ ዘዴዎች ላይ የሚደርሰው አደጋ ተመሣሣይነት ያለው ነው። ለዚህ ገለፃችን፤ አንዱ የሆነውን በመኪና ላይ የሚደርሰው አደጋ፤ በምሣሌነት እንመልከት፤

<u>የመኪና አደጋ በክፉ መንፈስ አማካኝነት የሚደርሰው፤</u>

- ክፉው መንፈስ አሽከርካሪውን ማለትም ሾፌሩን ማዕከል አድርጎ ሲይዝ፤
- የመንፈሱ የጥፋት ልጆች መኪናውን ሲሳፈሩ፤
- ደም የለመዱ የሰይጣን መንፈሶች በመኪና መንገዶች ላይ ሰፍነው ሲገኙ ነው።

ሹፌሩ <u>የቤተሰብ የዛር መንፈስ ሲኖርበትና</u> በራሱ ገንዘብ ዶሮ፣ ዕጣን፣ ሰንደል ሽቶ ወዘተ... እየገዛ በመስጠት መንፈሱን የሚገብርና የሚያስገብር ሆኖ ይቆይና ከጊዜ በኋላ፤ በተለያየ ምክንያት

<u>ግብሩን ሲቀንስ፣ ሲዘነጋና ሲያቋርጥ</u>፤ መንፈሱ ተቆጥቶ የመኪና አደጋ በማድረስ፤ ግለሰቡን ይቀጣዋል።

በዚህም፤ የአሽከርካሪው ጠስ የአዙሪት መንፈስ ሆኖ፤ መዘዙ ለተሣፋሪዎቹ በሙሉ ይተርፋል፤ ማለት ነው። የአደጋው ክባድነትና ቀላልነት የሚወሰነው፤ ሾፌሩ መንፈሱን ባስቆጣበት የጥፋት መጠን ልክ ይሆናል።

ከዚህ በተቃራኒው፤ <u>ሾፌሩ የዘር መንፈስ እንዳለበት ሳያውቅ</u> ይቀርና በሥራውና በኑሮው ላይ ብቻ ሲያተኩር፤ ግብሩን ያላገኘውና ውስጡ የተደበቀው ክፉ መንፈስ በመቆጣት፤ በማሽከርከር ላይ እንዳለ ልቡን ሰውሮ አደጋ ያደርስበታል።

በዚሁ መሠረት የተቆጡት መንፈሶች በሾፌሮችና በተሣፋሪዎች ላይ ከሚያደርሱት አደጋዎች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት፤

- ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው፤ ደም የለመዱ መናፍስቶች በመንገድ ላይ በመሰፈን፤ በቋሚነት መኪና በመገልበጥ፣ ትራፊክ መስለው በመቆም ቀጥታና ኩርባ መንገዶችን አስቶ ገደል ውስጥ በመክተት፣ ከግንብ፣ ከድልድይ፣ ከግንድ፣ ከቆመ መኪና ወይም ከሌላ ግዑዝ አካል ጋር ወዘተ... በማጋጨት፤ ሕይወት እንዲጠፋና ደም እንዲፈስ ያደርጋሉ።
- የሾፌሩ የጫት፣ የሺሻ፣ የሐሺሽና የመጠጥ የሱስ መንፈሶች ግብራቸውን በበቂ ሁኔታ ካላገኙ፤ እንደተናቁና እንደተጠሉ በመቁጠር፤ አደጋ ያደርሳሉ። ከዚህ በተቃራኒው በሾፌሩ ሕይወት የሚቀና የምቀኛ <u>የመተት መንፈስ በሰውየውና በመኪናው ላይ የተላከ ከሆነ ደግሞ፤</u> ግለሰቡ ከላይ በተጠቀሱት የሱስ ዓይነቶች ሐሊናው ናውዞና ተሸበቦ፣ ልቦናውና ዓይኑ ተጋርዶ፤ ለአደጋ ይጋበዛቃል።
- <u>ለምሳሌ፦</u> በመንፈሱ ተጽዕኖ አሽከርካሪው መሪንና ፍሬንን መቆጣጠር ተስኖት፤ መኪናው እንዲጋጭ፣ እንዲገለበጥ፣





ገደል እንዲገባ፣ ሌላ አደጋ እንዲያደርስ ወዘተ... በማድረግ፤ ጥቃቱን በከፋ ሁኔታ ይገልጣል።

- አንዳንድ ሾፌሮች፤ በሥራ ምክንያት ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ሲጓዙ፤ ከብዙ ሴቶች ጋር በሚፈጽሙት ዝሙት የተነሣ፤ በቀላሉ በቡዳ መንፈስ ተይዘው፤ መንፈሱ ልቦናቸውንና ዓይናቸውን በመሰወር፤ አደጋ ሊያደርስባቸው ይችላል።
- በመጀመሪያ ደረጃ፤ ባለቤቱ መኪናውን በሚርትና በስልብና ገንዘብ ከገዛው፤ እንዲሁም፤ የግንርው ግንኙነት ከጠንቋይና ከመተት ጋር የተነካካና የተያያዘ ከሆነ፤ ያ መኪና ለአደጋ የተጋለጠ ይሆናል ።
- በመኪናው ውስጥ አደገኛ የጥፋት መንፈስ ልጆች ከመንገደኛው ጋር አብረው ተሣፍረው ሲገኙ፤ በእነርሱ ላይ ያደሩት ክፉ መንፈሶች በሹፌሩ ላይ አዚም ሆነው ስለሚገቡ፤ የመኪናው አደጋ ቅርብ ይሆናል ማለት ነው።

ከዚህ <u>ለየት ያለው ሌላው ጥቃት</u> ደግሞ፤ አዲስ መኪና ሲገዛ ወይም አገልግሎት እየሰጠ ያለም ቢሆን፤ የመኪናው የሞተር፣ የነዳጅ፣ የኤሌክትሪክ መስመር ወዘተ... ላይ የሚያርፍና የሚቀመጥ <u>የምቀኛ የመተት መንፈስ</u> ተልኮበት፤ በክፉው መንፈስ ኃይል አስገዳጅነት ተሽከርካሪው እንዳይንቀሳቀስ ሊያደርገው ሁሉ ይችላል።

## በዓውደ ዓመትና በበረከት ወቅቶች፤ የሚቆጡና የሚነሱ የዛር መንፈሶች

**‹‹ጠላቶችህ በበዓልህ መካከል ተመኩ፤ የማያውቁትንም ምልክት ምልክታቸው አደረጉ። . . . ኑ፣ የእግዚአብሔርን በዓሎች ከምድር እንሻር አሉ።›› መዝ. 73 (74) 4-9**

የሰው ልጆች የሚደሰቱበትንና በእግዚአብሔር ቸርነት በረከትን የሚያገኙበትን ወቅቶችና የዓመት በዓል ጊዜያትን ጠብቀው፤ ቁጣቸውን የሚገልጡና መዓታቸውን የሚያመጡ የዛር መንፈሶች ብዙ ናቸው።

በመጀመሪያ ደረጃ ለመቆጣትም ዕድሉን የሚያገኙት በሕይወታችን ላይ የወህኒ ያህል እስራቱን ስላጠነከሩና ቦታ ስለተሰጣቸው ነው።

መንፈሶች ከዚያም በላይ፤ በእርእየ ሥላሴ ከተፈጠረው ሰው በላይ አቅምና ጉልበቱን አጥብቀው በመያዝ፤ ሕይወትን በመለማመድ፤ የሚጠይቁት ግብር ካልተሟላና ከጥያቄያቸው መካከል አንዱ ቢጎድል እንኳን፤ የከፋ ቁጣቸውን ባደሩባቸው ሰዎች ላይ የሚገልጡ ቂመኛ መንፈሶች ናቸው።**‹‹ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወህኒ ሊያገባችሁ አለዉ››ይላል። ራእይ 2፥10**

### የቁጣው መግለጫ ወቅቶች፤

**ሀ. ከግንቦት ጀምሮ ሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ ወር ድረስ፤**

**‹‹ለዚህ ሕዝብ ግን የሸፈተና ያመጸ ልብ አላቸው፤ ዓምፀዋል፣ ሄደውማል።›› ት/ኤር 5፥23**

እነኚህ ወራት አምላካችን እግዚአብሔር ክረምቱንና ዝናሙን የሚያመጣልን ወቅት በመሆኑ መንፈሶቹ፤ የክረምት መግቢያው በጣዖት የረከሰ እንዲሆን በማድረግ በረከትና ረድኤት የራቀው ዘመን ሆኖ እንዲቀጥል ጥፋታቸውን ይገልጣሉ።





ዲያብሎስ የቁጣው ኃይል እንዲገለጥ፤ በእግዚአብሔር የቸርነት መንፈሳዊ ስጦታ ላይ ያለውን ቅናትና ተቃውሞ ለመግለጽ የክረምቱን ወቅት ለማዛባት ሠራዊቱን በእነዚህ ወራት ያንቀሳቅሳል።

**ለ. ከጳጉሜ ጀምሮ መስከረምና ጥቅምት ድረስ፤**

በአዲስ ዓመት በእግዚአብሔር የመታደስ ስሜት የሚፈጠርበትና የሚታይበት በአብዛኛው ሰዎች ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገው የሚንቀሣቀሱበት ወቅት በመሆኑ የተቆጡት መንፈሶች በነዚህ የዘመን መለወጫ በዓል አካባቢ ይነሳሉ። **‹‹ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፣ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሰራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ስልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፣ በፊቱ ተመላለሳችሁባቸው።›› ኤፌ. 2፥2**

**ሐ. ሕዳርና ታህሳስ፤**

ሰዎች ሰብላቸውን የሚሰበስቡበትና ጎተራቸውን በእህል የሚሞሉበት የበረከት ጊዜ በመሆኑ፤ ይህ ፈጣሪያችን ለሰዎች የሰጠውን በረከት በመቃወም መንፈሶቹ፤ ከፍተኛ ቅናትና ምቀኝነት የሚያድርባቸው ስለሆነ፤ በዚህ የመኸር ወራት ለጥፋት ይሰለፋሉ።

ይህን ክፋት የሰነቀው የክፉው መናፍስት የዛር ቁጣ በራሱ የጥፋት መንገድ ያሰራቸውን ሰዎች ሁሉ፤ ከላይ የተጠቀሱትን ወቅቶች እየጠበቀ የእግዚአብሔርን ጸጋና በረከት ያጎድልባቸዋል።

### የዛሩ የቁጣ መግለጫዎች፤

- በቂ የደም ማፍሰስ ሥርዓትና ግብር ካልተደረገለት፤
- ለእርሱ ክብር፤ የተለየ ቀለም ያላቸውና እንዲለበሱለት የሚፈልጋቸው አልባሳት ካልተሟሉ፤

- ልዩ ልዩ መዓዛ ያላቸው የሚወዳቸው ሽቶዎች ካልተዘጋጁለት፤
- የተለያዩ የተንኮልና የክፋት ጠባያትን የወረሱት ሰዎቹ፤ ቤተሰባቸውንና ልጆቻቸውን ካልረገሙና ካላበሳጩለት፤ በከፍተኛ ቁጣ ይነሣል።

እነዚህን ግብሮቹን በችግር ማለትም በአቅም ማነስ፤ በአልባሳት እጦት፤ መንፈሱን በመናቅና ባለመቀበል ወዘተ... የተነሳ ሳይሟሉ ሲቀሩና ችላ ሲሉት፤ ልክ የዓመት በዓልና የደስታ ወቅቶችን ጠብቆ፤ ባልና ሚስቶችን ያጣላል፤ እናትን ከልጇ፤ ልጅን ከአባቱ ወዘተ... ያጋጫል። ያለያያል።

<u>ለምሳሌ</u>፤ የቤተሰብ አባላቱ የቅዱስ ዮሐንስ በዓልን በደስታ እንዳያሳልፉ ጸብና ሁከት ይቀሰቅሳል። ከቤተሰቡ መካከልም አንዳንዶቹ በበዓሉ ዋዜማ ከቤት እንዲወጡ ያደርጋል። ይህ የዲያብሎስ ቁጣ ነው። ዛሩ ራሱን የቤቱ አባወራ አድርጎ ስለሾመና ሰዎቹም ስለተቀበሉት፤ የዓመት በዓል ሥርዓቱ በእርሱ ፍላጎት እንዲመራ ይፈልጋል። ከእርሱ በተቃራኒው የሚንቀሳቀሰውን ነገር ሁሉ ስለሚቃወም፤ ቁጣውን በሁከትና በሕመም ይገልጣል።

የጸብና የሁከት መንገዱ ካልተሳካለት ደግሞ ሌላ አማራጭ ይፈልጋል። ከእነዚህም መካከል አንዱ ባደረበት ሰው አካል ላይ ሕመም መፍጠር ነው። እንዳይመቸውና ዕረፍት እንዳያገኝ አድርጎ ጠቅላላ ሰውነቱን ያሳምመዋል፤ ራሱን ሁለት ከፍሎ ከባድ ራስ ምታት ያመጣበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ ዛሩ በአካል ላይ የሚያደርሰው አደጋ የተለያየ መሆኑ ነው። አንዳንዶችን አለ ዕድሜያቸው ዓይናቸውን ማጥፋት፣ የልብ ሕመም ወይም የአካል ቁርጥማት ማድረስ ወዘተ... ተከታታይ የመንፈሱ ዋንኛ ጥቃት ነው። በዚህም ጉዳቱን ብዙዎች የቤተሰብ የዘር ችግር ነው ብለው እንዲቀበሉት ያደርጋል።





ሌሎች ተመሳሳይ ሕመሞችንም እየፈጠረ፤ ቤተሰቡ በዓሉ በዓል ሳይመስለው በብስጭትና በንዴት የዓመቱን መጀመሪያ ቀን ‹‹ሀ›› ብሎ ይከፍትላቸዋል። በዚህም የተነሣ ግለሰቡ፤ ‹‹ **በቃ ይሄ ዓመት ለእኔ አይሆነኝም!**›› ብሎ በሚሚረት፤ ሌላ ሰይጣን ጎትቶ፤ የሚርት መንፈስን ጠሪና አስገቢ እራሱ ይሆናል።

ዛር ደግሞ ሌሎች ክፉ መንፈሶችን በፍጥነት የመሳብና የማስገባት ጠባይ ያለው በመሆኑ፤ ዲያብሎስም፤ ሰውየው በብስጭት <u>የእኔ አይሆንም</u> ብሎ የተናገረውን የሚርት ምሪት ተቀብሎ፤ ዓመቱን ሙሉ ግለሰቡን እየተከተለ መከራውን ያሳየዋል።

‹‹እገሌ ሚስቱን በበዓል ምድር ከቤት አስወጣ። ልጁን በአውደ ዓመት ምድር ከቤት አባረረ›› እንላለን።

የችግሩ ሥርና ምንጭ ግን፤ ቤታችን ውስጥ ጥላቻን፣ ጸብን፣ ሁከትንና አመጽን ወዘተ... ይዞ የገባና የተቆጣ የክፉ ጠላት መንፈስ በመኖሩ ነው።

አንዳንድ ሰዎችና ቤተሰቦች ዓመት በዓል ሲመጣ፤ ይጨነቃሉ፤ ይጠበባሉ። የጭንቀታቸው መንስኤ ደግሞ ገንዘብ ማጣት ሳይሆን፤ ‹‹ **ይሄ በዓል ደረሰ! መዓቱንና በሽታውን ሊያመጣብኝ ነው! ደግሞ ምኑን ሊያመኝ ነው?**›› በማለት ደስታ ከድቷቸው እንዲያሳልፉ ያደርጋል።

የሚገርመው ግን፤ በዓሉና የበረከቱ ወቅት ካለፈ በኋላ፤ ሕመሙም ሆነ የሁከቱ ችግር የመጥፋቱ ጉዳይ ነው። በዚህ የተነሳ ሰዎች፤ ቋህንን ከመሰለ ሥቃያቸው ለመገላገል፤ ሀብታቸውን፣ ገንዘባቸውንና እንስሶቻቸውን ሣይቀር ለክፉ መንፈስ ያካፍላሉ፤ ይገብራሉ። የተገበረው መንፈስ ደግሞ፤ የገበሩትን ሁሉ ለጊዜው በማስደሰት በረዥም ጊዜ ዕቅዱና በምላሹ ጠላትነቱን በማጠንከር፤ ልጆቹ አድርጎ ይይዛቸዋል።

የቀደሙት ቤተሰቦች ሲያልፉና በእነርሱ እግር የተተኩት ልጆቻቸው፤ የተለያዩ የውርስ መንፈሶች ሰለባ በመሆን፤ በመናፍስቱ ወህኒ ቤቶች ውስጥ ታጉረው የሚማቅቁ ጽኑ እስረኞች ይሆናሉ።

የቁጣ መንፈሶች ከዚህ በተለየ ሁኔታ፤ ቀደም ሲል ያልነበረና የሌለ ሱስ እንዲፈጠር፤ ወይም የተቋረጠ ሱስ እንዲያንሰራራ ያደርጋሉ፤ ይቀሰቅሳሉ። ጠጥተን የማናውቀው፣ አሲያም የምንጠላው ቡና፣ አልኮል መጠጥ፤ ቢራ፣ ጠጅ፣ ጠላ ወዘተ... በሚያስገርም ሁኔታ፤ ሲያምረንና ሲያሰኘን ይችላል። በአፍንጫ ላይ አንዳንድ ጊዜ የማንፈልገው ዓይነትና የሌለብን የሱስ አመል ውል እንዲልብን በማድረግ ይቀሰቅሳል። ለምሳሌ የሲጋራ፣ የክብሪት፣ የመኪና ወዘተ... ጭስ ለማሽተት ልንፈልግ ሁሉ እንችላለን።

ይህ ውስጣችን የገባው ክፉ መንፈስ ፍላጎት እንጂ፤ የቀደመውና የነበረው የራሣችን አመል ላይሆን ይችላል።

የመናፍስቱ ውጊያ በዝናም ወቅት ሲያይል፤ በርካታ ሰዎች የብዙ አስማተኞችን፤ ጠንቋዮችንና መተተኞችን ቤት በክረምት ያንኳኳሉ፤ ይጎበኛሉ።

ያልተገነዘቡት ትልቁ አደጋ ግን፤ በክረምት መግቢያ ላይ የሚላኩ መንፈሶች፤ የመጨረሻ ከባድ፣ አደገኛ፣ ጸጋና በረከትን የሚያሸሹ፣ ሁከትንና ጸብን የሚወልዱ፤ ውስብስብ ጠባይ ያላቸው፤ መሆኑን ነው። **መጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ ወንጌል 24 ላይ ‹‹በዚያችም ወራት ለእርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው። ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ።››**

<u>ክረምት ለምን</u>? ክረምት በርቀት የምናይበት ዓይናች የሚደክሙበትና በአካባቢያችን ላይ ብቻ ተወስነው የሚቆዩበት፣ ንጹህ ውኃ የሚደፈርስበት፣ ከዚያም በላይ ደግሞ መሬት ፍሬዋን ለመያዝ ዕድሉን የምታገኝበትና የምትዘጋጅበት ምልክትና ወቅት በመሆኑ ምቀኛው ሰይጣን፤ የሚቃወመው ወቅት ነው።





<u>ሰንበት ደግሞ</u>፦ የማረፊያ ቀን፣ እግዚአብሔርንና ቅዱስ ሥራውን ማመስገኛ፣ መቀደሻ፣ የደግነትና የበረከት ሥራዎችን ለእግዚአብሔር የምናቀርብበት፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ የሠራነውን ለስሙና ለክብሩ፤ ተገዝተን የምንባረክበት ዕለት ስለሆነ፤ ዲያብሎስ በቁጣ የሚንቀሣቀስበት ቀን በማድረግ በጠብ ወይም በሌላ የጥፋት ዘዴ ሲለውጠው አይገባንም።

<u>ለእርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮውላቸው ለምን ተባለ?</u> ዓመጻን፤ ክፋት፤ ተንኮልን፤ እሹሩሩ የሚሉ፤ በሆዳቸው ግፍን፤ ምቀኝነትን፤ በሌሎች ሕይወት ላይ አደጋ ለመሰንዘር ዕቅድ ማውጣትን፤ በመተትና በሟርት መንፈስ ሄደው ሌላውን የማጥፋት ሃሣብን በልቦናቸው ውስጥ ይዞ መመላለስ፤ <u>እርግዝና</u> ይባላል።

በተጨማሪም፤ አመጻና ግፍ ላረገዙ የሌሎችን ጉዳትና ውድቀት ለማየት የሚጓጓ፤ በአስማትና በሟርት መንገድ አልፈው፤ ለሌሎች፤ ችግርና ሞት ለመደገስ የተዘጋጁም፤ <u>እርጉዞች</u> ይባላሉ።

<u>ለሚያጠቡ የተባለውስ?</u> ዕለት በዕለት ግፍ የሚናገሩ፤ ተቺ፤ ተቃዋሚ፤ ፊዘኛ ሆነው የሚኖሩ፤ በሌሎች ሕይወትና ኑሮ ውስጥ በገንዘብ፤ በጉልበትም ይሁን በመናፍስት ኃይልና እገዛ በምቀኝነት ጣልቃ ገብተው ተንኮልና ግፍን በማዳበር፤ ዲያብሎስን የሚያገለግሉና ሰይጣንን የሚደግፉ፤ ሁሉ <u>የሚያጠቡ</u> ይባላሉ።

ዲያብሎስ ስምና ክብር፤ በመልክና በቀለም፤ በበግና በዶሮ ዓይነት እየተለየና እየታረደ፤ ይሄኛውን ለዚህ ወር፤ ያኛው ለዚህ ወቅት እየተባለ፤ በመንፈሱ ቋንቋ ‹‹ጭዳ›› እየተደረገ እንስሳት ሳይቀሩ፤ ክፉ መናፍስት ማጠናከሪያና ገጸ በረከት ሆነው እየቀረቡ፤ ለዘመናት ከሰይጣን ጋር አብረን ኖረናል።

**‹‹የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።›› ኤፌ. 1፥17**

ከሰው ልጆች ኃይልና ጉልበት በላቀ፤ በራሳችን አስተዋጽኦ ዲያብሎስ ከፍተኛ ጥንካሬ አግኝቶ ከራሱ ጋር አደራጅቶናል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን መደራጀት የማይፈቅደው መጽሐፍ ቅዱስ፤‹‹የሰይጣን ማህበር ናቸው›› ሲል ይገልጻል፡፡ ራእይ 2÷24

በአጠቃላይ የዓመት በዓላትና የበረከት ወቅቶችን ጠብቀው የሚቆጡና የሚነሱ የዛር መንፈሶች፤ የእንስሳትንና የሰው ልጆችን ደም እንደግብር የሚጠይቁ፤ ቁጣ እንዲመጣ ማለትም በረዶ፣ መብረቅ፣ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ወዘተ... የመሳሰሉ በኃጢአትና በበደል ርኩሰት ምክንያት የተፈጥሮ አደጋዎች እንዲከሰቱ፤ በተቃራኒው፤ በክረምት ወቅት የዝናም መጠን እንዲያጥርና እንዲጠፉ የሚያሟርቱ፤ እንስሳት ካልተገበሩ በተለይ ከብቶች እንዲጎዱ፤ የሕብረተሰባችን ባህሎችና ልዩ ልዩ ልማዶች ተመሳስለውና ተንተርሰው በሰው ላይ የሚንሰራፉ፤ ክፉ መንፈሶች ናቸው፡፡

‹‹ጥፋት መቶአል፤ ሰላምም ይሻሉ እርሱም አይገኝም፡፡ ድንጋጤ በድንጋጤ ላይ ይመጣል፣ ወሬም ወሬን ይከተላል፣ ከነብዩም ዘንድ ራዕይን ይሻሉ፤ ከካሕኑም ዘንድ ትምህርት፣ ከሽማግሌዎችም ዘንድ ምክር ይጠፋል፡፡›› ት/ሕዝ ምዕ. 7÷25





## የጨሌ መንፈሶች

‹‹ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፣ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል፣›› ማቴ. 15÷8-9

ሰዎች የሰይጣን መንፈስን በመጥራት ከሚገናኙባቸው መንገዶች መካከል፤ የጨሌና የአቴቴ ሥርዓቶች በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

እነዚህም መንፈሶች እንደሌሎች ተመሳሳዮቻቸው ሁሉ የሚፈልጉት የግብር ዓይነቶች፤ በቅቤ በደንብ የላመ ምግብ፣ ቡና፣ አልባሳትንና ሌሎች ጥያቄዎቻቸው ከተሟሉ በኋላ፤ መንፈሱ ያደረባቸው ሰዎች የተለያዩ ቀለማት ባላቸው ጨሌዎች በማጌጥ፣ ለዲያብሎስ ተንበርክከው ትከሻዎቻቸውን በጨሌ እያሰነኩና በከንፈራቸውም እየሳሙ፤ መንፈሱን ጠርቶ በመገናኘት፤ የሰይጣንን ርዳታና እገዛ ይለማመናሉ፡፡ ለምሳሌ ፍላጎታቸው ልጅ መውለድ ከሆነ፤ ክፉው መንፈስ ልጅ እንዲሰጣቸው እምላኬ ጌታዬ እያሉ እየጠሩ ይለምኑታል፡፡

የጠያቂዋ ማሕጸን በመንፈሱ ቀድሞ የተዘጋ ከሆነ፤ ግብሩንና ሥርዓቱን ያለማቋረጥ ከገበሩለት የያዘውን ማህጸን ለቀቅ አድርጎ እንድትወልድ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የሚወለደው ልጅ ግን በክፉው መንፈስ የተያዘና የተጎዳ አእምሮና አካል ይዞ ወደዚህ ምድር ስለሚወጣ፤ ምሪቱ የሰይጣን በመሆኑ ውጤቱ አሳዛኝና አስከፊ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ የጨሌ ሥርዓት ላይ ሌሎችን ለመጉዳት ሲባል የሚደረግ የርግማን ልመናም ለዲያብሎስ ይቀርባል፡፡

### የጨሌ መንፈስ፤ ለልጆቹ የሚያወርሰው ጠባያት፤

- ለኑሮዋቸው ባለቤት አይደሉም፤
- የልጆቻቸው እናትና አባት አይደሉም፤ በባሕርይ መንፈሱ ይከፍላቸዋል፤

- ኑሯቸውና ቤታቸው ውስጥ በረከት የለውም፤
- ቢበሉ አይጣፍጣቸውም፤ ቢጠጡም አይረኩም፤
- ተደማጭነት የላቸውም፤ ቃላቸው መራራ ነው፤
- መናፍስቱ ክብራቸውን ገፈዋቸዋል፤ የክብር ሞገስ ያጣሉ፤
- ቤተክርስቲያን አይወዱም፤
- አንዳንዶቹም፤ መቃብር ላይ ስለሚጥላቸው፤ቀብር ሥርዓት ላይ እንዲገኙ መንፈሱ አይፈቅድላቸውም።
- ተልባና የፍየል ሥጋ መብላት አይፈቀድላቸውም፤ ከበሉ ግን፤ ሕመምና የዛሩ የቁጣ ቅጣት ይጠብቃቸዋል።
- ልጆቻቸው ቢማሩ አይገባቸውም፤ ሥራ መሥራትም አይወዱም፤

በአጠቃላይ ኑሯቸውንና ቤታቸውን የሚመራው የጨሌው መንፈስ ሰይጣን ስለሆነ፤ ሕይወታቸው ከነቤተሰባቸው ሰላም አይኖረውም። የመከራና የአበሳ መንፈስ ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ፤ ጥቃቱ እስኪነቃበትና በእግዚአብሔር መንፈስ እስኪያዝ ድረስ፤ ይቀጥላል። «እናንተስ ስለወጋችሁ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለምን ትተላለፋላችሁ? » ማቴ. 15:3

በአገራችን አንዳንድ አካባቢዎች እነዚህን የጨሌና የአቴቴ ሥርዓቶች ከባሕልና ከልማድ ጋር በማያያዝ ጎጂ እንዳልሆኑ ተደርጎ ይወሰዳል። እውነታው ግን ከዚህ ልማዳዊ አመለካከት ፈጽሞ የራቀ ከፉ መናፍስትን እየጠሩ የመገናኘት ሥራ መሆኑ፤ ሊታወቅ ይገባል። እግዚአብሔር ግን ለእኛ ያለው ሐሳብ በወልድ በኩል፤

«በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው።» ኤፌ. 1፥10

«ይኸውም፣ በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው።» ኤፌ.1፥12





## 1.2 የ<u>ዓይነ-ጥላ መንፈስ፤</u>

ዓይነ ጥላ፤ በምናየው፣ በምንረዳው፣ በምንገነዘበው ወዘተ... መንገዳችን ላይ፤ <u>እሽምቅና ተደበቆ ጉዳት</u> የሚያደርስብንና የሚያርፍብን፤ የክፉው መንፈስ ጥላ ዋንኛው የዲያብሎስ ኃይልና የጥቃት ክንድ ነው።

የዓይነ-ጥላ መንፈስን ልዩ የሚያደርገው፤ በመጀመሪያ ደረጃ በውስጣችን ሲገባ፤ ከጠባያችን ጋር <u>መመሣሰል</u> መቻሉ አንዱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ፤ ተምረን፣ ጥረን ግረን የት እንደምንደርስ፣ እንዴት እንደምናድግና ዕድላችን እንዴት እንደሚቃና፤ አስቀድሞ <u>የማወቅና አርቆ የማየት</u> ከፍተኛ ችሎታ ያለው መንፈስ መሆኑ ነው።

በተለይ ይህ ከራሣችን ጠባይ ጋር የመመሣሰሉ ጉዳይ አብሮን ኖሮ አብሮን ስለሚያድግ፤ ጨርሶ መንፈሱ በውስጣችን ስለመገኘቱ፤ ምንም ዓይነት መረጃ እንዳይኖረን ያደርጋል።

በመሆኑም፤ የዓይነ-ጥላ ሰይጣን በሕይወት ጎዳናዎቻችን ላይ፤ <u>ምንጊዜም ከፊት እየቀደመ፤</u> በኑሮዋችን፣ በሥራችንና በእውቀታችን ወዘተ...ላይ ሁሉ፤ <u>ዕንቅፋት</u> በመሆን፤ የሚያሰናክልና የሚያጨናግፍ ርኩስ መንፈስ ነው።

ዓይነ-ጥላ፤ የምታስበውን፣ የምታቅደውን፣ ከውስጥ ወደ ውጭ የምትይዘውንና የምታየውን በአኗኗርህ፣ በትምህርትህና በሥራህ የምታገኘውን በረከቶች ሁሉ፤ ማለትም፤ ዕድገት፣ ሽልማት፣ የማዕረግ ዕድገት፣ መልካም ነገር፣ ጥሩ ዕድል ወዘተ... <u>አትኩሬት ሰጥቶ የመከታተል</u>፤ ጠባይ ያለው መንፈስ ነው።

ሌላው የሌሊት ዳሰሳ በማድረግና በማስደንገጥ፤ የከበደ ነገር ሆኖ በመጫን፣ ድንገት የልብ መምታትና መበርገግ፣ ብርድ ብርድ የማለት ስሜት፣ መኝታን፣ የውስጥ ልብስን፣ ጓዳንና ሳሎንን፤ በክፉ ጠረን ድንገት መለወጥ፤ ግራ የሚያጋቡ ዘዴዎቹ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም፤ ዕቃና ገንዘብን በድንገት መሰወር፤ የዚህ መንፈስ ልዩ ሴራ ነው። በዚሁ መሠረት፤ የመንፈሱ ውጊያ፤ <u>በሁለት አቅጣጫዎች</u> ይገለጣል።

ሀ. <u>ዕንቅፋት መፍጠር፤</u>

የኑሮ ወይም የሕይወት መንገዶቻችን በሙሉ <u>መከራና ዕንቅፋት</u> የሞላበት እንዲሆን ያደርገዋል። ምክንያቱ በግልጽ የማይታወቅ፤ የብቸኝነትና የትካዜ ስሜት፤ ሐዘንና ለቅሶም ያመጣል።

ለ. <u>ጥሩ ውጤትን ማበላሸት፤</u>

እንደምንም ብለን ዕንቅፋቶቹንና ችግሮቹን ተቋቁመን በማለፍ ጥሩ ውጤት ብናስመዘግብ እንኳን፤ ባስገኘነው ፍሬ ነገር ላይ፤ <u>አልፎ ሄዶ በማረፍ</u>፤ ድካማችንን ከንቱ ያደርገዋል።

የዓይነ-ጥላ መንፈስ፤ <u>አካላዊ ጤንነትህን</u> በቀጥታ አይጎዳም፤ አይተናኮልም። እጅህን፤ እግርህን፤ ዓይንህን ወዘተ... አይዝም። የእርሱ ጉዳይ፤ <u>አእምሮህና ልቦናህ ውስጥ ገብቶ፤ ማስጨነቅና ማሰቃየት ነው</u>። የሐሳብ ጦርነት ውስጥ መክተት ነው።

በመሆኑም፤ የስኬት አቅጣጫህን በአርቆ ማሰብ ችሎታው ስለሚያውቀው፤ መሠረታዊ በሆነ አንድ ዋና ነገር ላይ ያተኩራል።

መሠረታዊ የሆነው አንዱን ዋና ነገር ካበላሸ ደግሞ፤ ሌላው የኑሮ አቅጣጫህ በሙሉ በራሱ ጊዜ እየተበላሸ እንደሚሄድ እርግጠኛ ይሆናል። ይህ የመንፈሱ የረቀቀ ሥሴትና የነጠረ ሥልት ነው።

ከዚህ በተጨማሪም፤ እንደ ዛር መንፈስ ሁሉ ዓይነ-ጥላም፤ ሌሎች ክፉ መንፈሶችን በመሣብና በማስገባት የጥፋት መሠረቱን በሰውነታችን ውስጥ የሚያመቻች መንፈስ ነው።

አንዳንድ ጊዜ የዓይነ-ጥላ መንፈስ፤ ለብዙዎች ጠንቅና መከራ በሚሆኑ ሰዎች ውስጥ ገብቶ፤ ክፋትንና ምቀኝነትን ያስለጥናቸዋል።



በማለዳ መያ'ዝ

እነዚህን ለዓላማው ማስፈጸሚያ የሚጠቀምበቀቸውን ሰዎች፤ ትምህርትና ዕድላቸውን ለጊዜው አይነካም። ጭራሽ ይጠብቃቸዋል። በሥልጣንና በገንዘብ ከፍታም ያመቻቻቸዋል። ሰዎቹ ፍጹም እንዲያምኑትና ሌሎችም እንዲገዙላቸው፤ ሥራቸውን የሚያግዝ፤ ሃሣብ በሚማርክ ሁኔታ፤ ያቀርባል፤ ያመነጫል።

ሌሎችን ስለሚጎዱለትና በሰዎች ላይ የፈጸሙትን ክፋት እንደግብሩ በመቁጠር፤ ጊዜያዊ ዝናና ክብር ያጎናጽፋቸዋል። ለሌላ አዲስ ጥፋት ያበረታታቸዋል። የሚገርመው ግን፤ ሲገለገልባቸው የቆየውን እነዚህን ሰዎች፤ በመጨረሻ ላይ ራሱ በፈጠረላቸው ታላቅነት ቀንቶ፤ ሲያጠፋቸው መታየቱ ነው።

በሌላ አቅጣጫ ዓይነ-ጥላ ውስጥህ ቁጭ ብሎ ውጫዊ ሕይወትህ እንዲበላሽ የማዘዝ ኃይል አለው። የሚግባቡትን ያቃቅራል፤ የሚፋቀሩትን እሳትና ጭድ ያደርጋል፤ እልህ ውስጥ ይከታል፤ ከሜዳ ተነስቶ ጸብ ያስጭራል፤ ተናዳጅና አኩራፊም ያደርጋል።

ሌላው ደግሞ፤ የምትሄድበትን አቅጣጫ አስቀድሞ ስለሚያውቅ፤ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አልፎህ ሄዶ መንገድህ ላይ የተለያየ እንቅፋት ያስቀምጣል። ይህ ካልተሳካለት ደግሞ፤ መድረሻህ ላይ ገብቶ ተዘጋጅቶ ይጠብቅሃል።

<u>ይህንን በምሳሌ እንመልከተው</u>። ቢሮ ከሆነ፤ አንተ ውስጥ ያለው የዓይነ-ጥላ መንፈስ፤ ከአንተው ላይ ተነስቶ አለቃህ ውስጥ ቀድሞ ገብቶ ይጠብቅሃል።

ቢሮህ እንደደረስክ አለቃህ፤ ራስህን እስክትጠላ ድረስ፤ በከባድ ቁጣና ሞራል በሚነካ ዘለፋ፤ ያስተናግድሃል። የሥራህ ሕልውናም፤ ሊያከትም እንደሚችል በመግለጽ፤ ያስፈራራሃል፤ ያስጠነቅቅሃል። አንተም ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ትጀምራለህ። ወደ አካል ግጭት ሁሉ ልታመራ ትችላለህ።

መንፈሱ፤ አለቃህ ስላንተ ያለውን መልካም አመለካከት ማዛባት ብቻ ሳይሆን፤ ሙሉ ለሙሉ ሊያስቀይረው ሁሉ ይችላል።

ይህ የዓይነ-ጥላ መንፈስ ከራስህ ተነስቶ ሌላውን ሰው ማዘዝ ሲጀምርና ሲችል፤ አንተን ራስህን ከመልካም ሥነ-ምግባርና ከተወዳጅ ጠባይ ያፈናቅልሃል።

<u>ሌላ ምሳሌ እንመልከት</u>፤- ሚስት እቤት ቁጭ ብላ እግዚአብሔር አምላክን የሚያወድስ መዝሙር እየሰማች ነው፤ እንበል። በዚህም የተነሳ ውስጧ ያለው የዓይነ-ጥላ መንፈስ ምቾት ያጣል።

ሁኔታው በእንዲህ እንዳለ ባል ከውጭ ወደ ቤት ይገባል። ‹‹አንቺ ደግሞ ሁልጊዜ አለዚህ መዝሙር አትሰሚም እንዴ? በይ ይሄን አውጭና የእገሌን ዘፈን አድርጊ!›› ይላል።

በዚህ ጊዜ ሚስትየዋ ውስጥ ያለውና ምቾት ያጣው ርኩስ መንፈስ፤ ባልየው ባነሳው ተቃውሞ መካከል ባገኘት ጠባብ ክፍተትና ወርቃማ ዕድል ተጠቅሞ፤ በፍጥነት ወደ ሰውየው ይገባል። ወድያው፤ መንፈሱ ባልን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮት፤ ከሚስቱ ጋር እንዲጋጭ ያዘዋል። ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ለመገመት የሚያዳግት አይሆንም።

ይህ ከራስህ ተነስቶ ሌላውን የሚያዘው ርኩስ መንፈስ፤ በተመሣሣይ ጠባይ፤ <u>በአጋንንቶች ኅብረት</u> ማለትም፤ <u>ዛር- ዓይነ-ጥላ፣ ዛር-ቡዳ ወዘተ</u>… እያለ፤ <u>በተቀናጀ</u> ሁኔታ ሥልቱን እየቀያየረ መናፍስታዊ ውጊያውን ያጠናክራል።

ሌላው ችግር የሚያመጣብህ ደግሞ፤ <u>በዕድልህ ስምሪት</u> ላይ ነው። ሥራ ለመግባት ፈተና ለመወዳደር ስትሄድም፤ እንደዚሁ መንገድህ ላይ እንቅፋት ያበጃል። መቶ ጊዜ አጥንተህና ተዘጋጅተህ ብትቀርብም፤ በፈተናው ወቅት እያምታታህና ልቦናህን እየሰወረ፤ ውጤትህን ያበላሽዋል።

ፈተናውን ብታልፍ እንኳን፤ የሚያጨናግፍ ሌላ ያልገመትከው ችግር ይፈጥርብሃል። ‹‹ፈተናውን ያለፍክ ቢሆንም፤ በበጀት እጥረት





የተነሳ ይህንን ሥራ ሌላ ሰው ደርቦ እንዲሰራው ስለተወሰነ፤ የአንተ ቅጥር ተሰርዟል።›› ትባላለህ። ይህ አንድ ምሳሌ ነው።

ምክንያቱም፤ የዓይነ-ጥላ መንፈስ፤ መንገድህን ስለተረዳው፤ መልካም እንጀራህን አልፎና ቀድሞ ሄዶ ስለሚዘጋው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፤ እግዚአብሔር በሰጠህ በረከት ላይ ውስጥህ ያለው መንፈስ ቅናት ስለሚያደርበት፤ ዕድልህን እየዘጋና እያበላሸ፤ ከፈጣሪ አምላክህ ጋር ያለህን ግንኙነት ለማጥፋትና ለማቋረጥ ነው።

የዓይነ-ጥላ መንፈስ እርር ብግን ብለህ የምትበሳጭበትን፣ ራስህን እስከማጥፋት ድረስ የምትማረርበትን፣ ሞራልህ በከፍተኛ ደረጃ ወድቆ፤ በኪሳራ ሕይወት ውስጥ እንድትገኝ ውስጥህንና ውጭህን እያዘዘ፤ ተስፋ አስቆርጦና ግራ አጋብቶ ቀስ በቀስ የሚያጠፋህ መንፈስ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ‹‹እገሌ ምን ነክቶበት ነው፤ ራሱን ሰቅሎ የገደለው?›› ይላሉ። ‹‹አሁን ጥጋብ ይዟት እንጂ! ምን መድኃኒት የሚያስጠጣ ነገር አለ?›› እንላለን።

ጉዳዩ ግን ሌላ ነው። <u>ውስጣችን ሆኖ የሚገፋፋና የሚቀሰቅስ አደገኛ የርኩስ መንፈስ ኃይል</u>፤ በሕልውናችን ላይ ነግሷል። በዚህ የተነሳ የዓይነ-ጥላ መንፈስ በርካቶች፤ ሳያውቁት ሞታቸው በእጃቸው እንዲሆን አነሳስቷል፤ ያነሳሳል፤ ውስጣቸው ቁጭ ብሎም ያለማምዳቸዋል፤ ያሰለጥናቸዋል።

በመጨረሻም መንፈሱ መቶ በመቶ ሲቆጣጠራቸው፤ በመርዝ፣ በመድኃኒት፣ በጦር መሣሪያና በሥለት ወዘተ… ራሣቸውን ሊያጠፉ ይችላሉ። እያሽከረከሩ ከሌላ መኪና ጋር ሊጋጩ፣ ራሣቸውም በመኪና ሊገጩ፣ እነርሱም በመኪና ሌላ ሰው ላይ አደጋ ሊያደርሱ፣ ገደልና ባሕር ውስጥ ገብተው፣ ከፎቅ ተወርውረው ወዘተ… ሊሞቱ ይችላሉ። ብዙዎች እራሳቸውን የሚያጠፉበት ምክንያት ፤ በዚህ ክፉ መንፈስ ግፊትና ምሪት የተነሣ ነው።

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው፤ ይህ መንፈስ ያለባቸው ሰዎች፤ እራሳቸውን ባያጠፉ እንኳን፤ የሌላውን ሕይወት ለማጥፋትና ለማበላሸት እንዲችሉ፤ ውስጣቸው ያለው ርኩስ መንፈስ እቅዱን በስፋት ይዘረጋል።

ሌላው፤ በዓይነ-ጥላ የመቀደማችን ምልክቱ ደግሞ፤ በብቃት የተማርነው፣ የምናውቀው፣ ያስተማርነው፣ የሠራነው፣ ያሠራነው፣ ያቀድነው፣ የጠገነው ወዘተ... ሁሉ ድንገት ከአእምሮአችንና ከልቦናችን እልም ብሎ ጠፍቶ፤ ባዶ የማድረጉ ጉዳይ ነው።

በተለይ እውቀታችንን ሰውሮና ሰልቦ፤ ግራ ያጋባናል። ሌላው ሰው እስኪታዘበን ድረስ፤ ቅሌትና ውርደት ውስጥ ይከተናል። መሳቂያ፣ መሳለቂያም ያደርገናል።

ብዙ ሠርተን፣ ወጥተን፣ ወርደን ያለፍንበትን የተመሰከረለትን የቀደመውን ትምህርታችንንና ችሎታችንን፤ በአሉታዊነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል።

ወደ ልቦናችን ስንመለስ ግን፤ ምንድነው ያደረኩት? ምንድነው የተናገርኩት? ምን እየሆንኩ ነው? ብለን እንድንጨነቅ ያደርገናል። ተኝተን ብቻ ሳይሆን፤ ቆመንም እየሄድን ያቃዠናል። አንዳንዴ፤ እንዴ! ምንድነው ነገሩ? ብለን እንድናስብና ነገሩ ሁሉ እንዲደበላለቅብንና እንዲጨልምብን ያደርጋል።

ዛሬ የቀረውና እንደ ኋላ ቀርነት የሚቆጠረው፤ ዱሮ የቄስ ትምህርት ቤት እያልን እንጠራው የነበረው፤ የፊደል ገበታ ትምህርት ቤታችን ከተሰረዘ በኋላ፤ የመናፍስቱ ውጊያ <u>ከማስዳው</u> ጀምሮ አይሏል። ሰመ እግዚአብሔርን ማይጠራ ያደገው ትውልድ ዛሬ፤ ያለፈ ታሪኩና የወደፊቱ የኑሮው ብልሃቱ ጠፍቶታል።

በፊት የቄስ ትምህርት ቤት የኔታ ጋር ስንማር፤ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ቃሎች ያስደነግጡት የነበረው ክፉ መንፈስ፤ አብሮን ኖሮ አብሮን የተማረ ብቻ ሣይሆን፤ ከእኛ በላይ የተማረና የተለማመደ፤





በእኛ ላይ የሰለጠነ፣ ራሳችን ስለእኛ ከምናውቀው በላይ፤ ስለራሳችን የተሟላ መረጃ ያለው፤ አካሄዳችንንና አረማመዳችንን አስቀድሞ አውቆ የሚያዳክመን ይህ ጠላት ዛሬ፤ በራሣችን ድክመት ጥንካሬ አግኝቶ ቤቱን በላያችን ላይ ሰርቷል። እኛም፤ ከእግዚአብሔር መንገድ ወጥተን፤ ከአጥፊያችን ከዲያብሎስ ጋር ተባባሪ በመሆን፤ ሕይወታችንንና ዘመናችንን፤ በገዛ እጃችን፤ የመከራ አደረግነዋል።

## <u>የዓይነ-ጥላ መንፈስ በትዳርና በፍቅር ሕይወት ውስጥ፤</u>

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው፤ እንደ ዛር መንፈስ ሁሉ፤ የዓይነ-ጥላ መንፈስም፤ በወንዱ ውስጥ እንደሚስት፤ በሴቷ ወስጥ ደግሞ፤ እንደባል ሆኖ ይቀመጣል።

መንፈሱ ለወንዱ እጅግ በጣም ውብ የሆነች ሴት፤ በሕልሙና በእውኑ እያለ፤ ጎኑ እንደተቀመጠችና አብራው እንደተኛች አድርጎ ያሳየዋል። በተመሳሳይ ለሴቷም፤ መልከ-ቀመናው ያማረና የሚማርካት ዓይነት ሰው (ወንድ) ያሳያታል። ከዚህ በተጨማሪም፤ ቀደም ሲል አይተው የማያውቁት ነገር ግን፤ በገሃዱ ዓለም ውስጥ ያለን ሰው እንደዚሁ ለሁለቱም ያሳያቸዋል።

በዚህም የተነሣ፤ በማይጨበጥና በማይዳሰስ፤ በመናፍስቱ በተፈጠረ ዓለም፣ ሰዎች፤ ጨርሰው ከሌሉ፤ ከማያውቋቸውና ከማያስፈልጋቸው ሰዎች ጋር ፍቅር ይጀምራሉ። ባለትዳር የሆኑ ሰዎች በተለይ፤ ትዳራቸው አደጋ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ይህ መንፈስ ይፈታተናቸዋል። ዓይነ-ጥላ ባልና ሚስቱን ፈጽሞ እንዳይግባቡ አድርጎ፤ መኝታ እስከመለየትና ብሎም ጎጆዋቸውን እስከማፍረስ ያደርሳቸዋል።

ምክንያቱ ደግሞ ተደጋግሞ እንደተገለጸው፤ መንፈሱ ለእሱ እና ለእሷ በውስጣቸው ሌላ ሚስትና ባል ስለፈጠረባቸው ነው።

ከዚህ በኋላ፤ መንፈሱ ከላይ የተገለጹትን <u>የተዛቡ ድርጊቶችን</u>፤ ለማለማመድ፤ ሰዎቹ ራሣቸው ሌሊት ተኝተው፤ በሕልማቸው፤ ሲፈጽሙት ሊያሳያቸውና በመጨረሻም፤ ወደ ተግባሩ ይመራቸዋል። ‹‹እነርሱ ባለማወቃቸውም ጠንቅ በልባቸውም ደንዳናነት ጠንቅ ልቦናቸው ጨለመ፣ ከእግዚአብሔር ሕይወት ራቁ፤ ደንዝዘውም በመመኘት ርኩሰትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸውን ወደ ሴሰኝነት አሳልፈው ሰጡ።›› ኤፌ.4÷18

<u>በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን</u>፤ ከእምነታችንና ከባሕላችን መንፈሳዊነት የተነሣ፤ ይህንን <u>ተቃራኒ ጠባይ ለማስተናገድ ፈጽሞ ስለምንቸገር</u>፤ ብዙዎች ይህ መንፈስ ተጭኖ የሚያሰቸግራቸው ወገኖቻችን፤ ይህንን ሥቃያቸውን ለሌላ ሰው ለመናገር <u>ስለሚያሳፍራቸው</u>፤ ዘመናቸውን በሙሉ የመንፈሱ ጥገኛና ተገዢ ሆነው፤ ያሳልፋሉ።

የሕክምናና የሥነ-ልቦና ባለሞያ ዘንድ ቀርበው እንኳን፤ ይህንኑ ችግራቸውን ለመናገር <u>ስለሚያፍሩ፤</u> ‹‹ ምን እንደሆነ አላውቅም፤ በጣም ያስጨንቀኛል፣ እንቅልፍ ይከለክለኛል። ›› በማለት ያማክራሉ። ባለሙያዎቹም፤ ሙያቸው ስለሆነ ግለሰቦቹ በግልጽ ለመናገር ያልፈለጉትን ችግር ወድያውኑ ይረዳሉ። ችግሩን ለማቃለልም፤ <u>ሣይኮሎጂስቱ</u>፤ ተከታታይነት ያለው <u>የሥነ ልቦና የምክር አገልግሎት</u> ይሰጣል። <u>ሐኪሙ በበኩሉ</u>፤ የችግሩን ሁኔታ አገናዝቦና መርምሮ ሙያው በሚጠይቀው መሠረት፤ <u>በቂ ዕረፍትና ለቀናት የሚወሰድ የእንቅልፍ መድኃኒት ሊያዝ ወይም ሌላ የሕክምና ዕርዳታ ሊያደርግለት</u> ይችላል።

ሙያተኞቹ በዚህ ርዳታቸው፤ በሰዎቹ ውስጥ ያለውን <u>ርኩስ መንፈስ አረጋጉት</u> እንጂ፤ አላስወገዱትም። የሕክምናው ሙያ ስለባዎቹ ውስጥ ገብቶ <u>የሚያሳምመውና የሚያጨናንቀው</u> ኃይል፤





<u>ዲያብሎስ መሆኑን</u> ለመግለጽ፤ ምንም ዓይነት ተጨባጭ የሆነ ማረጋገጫ አይኖረውም። ስለዚህ፤ መናፍስታዊው ጉዳት ላይ ሕክምና ሙሉ በሙሉ መፍትሔ ለመስጠት አቅም ያጣል።

‹‹ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስ የሚመረምር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል፤ ርሱ ግን በማንም አይመረመርም።›› 1.ቆሮ 2÷14-15

መ. <u>የወሲብ ስሜትን የሚያዳክሙ መንፈሶች፤</u>

የወሲብ ስሜትን የሚያዳክሙ መንፈሶች፤ በሰዎች ጤናማ የጾታ ግንኙነት ላይ <u>አሉታዊ ተጽዕኖ ማሣደር</u> የሚችሉ የክፉው ጠላት የዲያብሎስ አካሎች ናቸው።

ይህን ድክመት ሊፈጥር የሚችለው አንዱ መንገድ፤ ጉዳቱን የሚያስከትሉ መንፈሶች ወደ ሰዎች <u>ተመትተው ሲላኩ</u> ነው። እነዚህ መንፈሶች ወደ ሰዎች ከገቡ በኋላ፤ ቀስ በቀስ ስሜትን ያዳክማሉ።

ክፉው መንፈስ፤ ሴቶች <u>የወሲብ ስሜት</u> ሙሉ ለሙሉ <u>እንዳይኖራቸውና እንዳያስቡት</u> ከማድረጉም በተጨማሪ፤ ወሲብ መፈጸምን ጨርሰው <u>እንዲጠሉ፣ ቢፈጽሙ</u> እንኳን፤ ለቀናትና ለወራት ያህል የሚያሰቃይ <u>ከባድ ሕመም</u> እንዲፈጥርባቸው ያደርጋል።

በተመሣሣይ ወንዶች ጨርሶ ስሜቱ <u>እንዳይኖራቸው</u>፣ ስሜቱ <u>ቢኖራቸው</u> እንኳን፤ ሚስታቸው ዘንድ ሲቀርቡ፤ <u>የዘር ፍሬ መዝሪያ አካላቸው አልታዘዝ</u> እንዲላቸው፤ ያደርጋል።

በዚህ የተነሣ በበርካታ ባለትዳር ጥንዶች መካከል፤ መቃቃርንና መለያየትን ፈጥሯል፤ ይፈጥራል። በተለይ ብዙ እህቶችና ወንድሞች፤ ባሎቻቸውና ሚስቶቻቸው ላይ የሚዩትን ይህንን ችግር የሚገነዘቡት፤ የክፉ መንፈስ አደጋ ከመሆኑ አንፃር ሣይሆን፤ እነርሱን ጠልተው ሌላ ሰው እንደወደዱ አድርገው በመውሰድ ነው።

ግን አይደለም። በአብዛኛው በተለይ ከጊዜ በኋላ የሚከሰቱ እንደዚህ ዓይነት ችግሮች አንዱ መንስዔያቸው፣ ክፉው መንፈስ የሚያስከትለው ጥቃት መሆኑ፣ ሊሰመርበት ይገባል።

## በቆነጃጅት ላይ የዓይነ-ጥላ ሴራ

ሀ. ቆነጃጅትንና ውብ ሴቶችን አለባል ማስቀረት፤

- ምርጫ ማብዛት፣ አቃቂር ማውጣት፣ በውበት መኩራትና መመጻደቅ፣ በፋሽን ምክንያት የሰውነት መገላለጥና በብዙ ወንዶች እይታ ውስጥ መግባት እንዲሁም በወንዶች የዓይን መንፈስ መያዝ፤

ለ. የቆነጃጅት የጥቅም ፍላጎት ቅጥ ያጣ መሆን፤

- ለፍቅረ ነዋይ መገዛትና የማያቋርጥ የሃብት መሻት በልቦና ውስጥ ማስቀመጥ፤

ሐ. ከጠንቋይና ከአስማተኞች ጋር ሩካቤ መፈጸም የሚያመጣባቸው ችግሮች

- በአስማተኛ ወይም በጠንቋዩ መንፈስ መታሰር፣ የተለያየ የማሕጸን ሕመም መፈጠር፣ የጠረን መለዋወጥ፣ የቃል፣ የሀሳብ፣ የድምጽና የአነጋገር ስልት መቀያየር፣ በዓይን የዝሙት መንፈስ መጠመድና በአንድ ወንድ አለመርጋትና የባልና ሚስት ፍቅር ድንገት ከልብ ውስጥ መጥፋት፤

## የመንፈሱ ግልጽ ውጊያ

- መንፈሱ ውበቷን ቀይሮ ለወንዶች ማሳየት፤
- ወንድ ሲያያትና ሲፈልጋት፣ ወንዱ በራስ ጭቃት መመታትና በቁርጠት ሕመም መያዝ፤
- በቀረቤታ ወቅት ደግሞ ወንዱን ሌሊት ማቃዠት፣ ማሳፈራራትና እንቅልፍ መከልከል፤





- የሩካቤ አካሉን ማዳከምና ፍላጎቱን ማጨለም፤
- የመኝታውን ጠረንና የቤቱን ሽታ ማበላሸት፣ መለወጥ፤
- ለወንዱ፣ የማትደፈር ቆንጆ አድርጎ ማሳየት፤
- ከአቅም በላይ አድርጎ ውበትን ማየትና እኔ ለእሷ አልሆንም በማለት ወንዱን ተስፋ ማስቆረጥ፤
- ወንዶች የወደፊቱን ሁኔታ በመገመት፣ ቆንጆ አግብቼ ምን እቃጠለኝ በማለት ምርጫን ማስቀየር፤
- ቆነጃጅት የኑሮ፣ የሥልጣን፣ የእውቀት ደረጃን እንዲመርጡ በማድረግ የጋብቻን ጊዜ ማሳለፍ፤ ዋንኞቹ የመንፈሱ ውጊያዎች ናቸው።

በተመሳሳይ ወንዶችም ያለ ሚስት ቆመው እንዲቀሩ፣ ይህ ክፉ መንፈስ እንደ ሴት እህቶች ሁሉ፣ መራጭና አቃቂር አውጪ ወዘተ... ያደርጋቸዋል።

በአጠቃላይ ዓይነ-ጥላ፣ በውጫዊ አካላችን ላይ በጉልህ የሚታይ የጤና እንከን አንዳንዴ ባያመጣም፣ አእምሯችንን በማድማት፣ መንገዳችን ላይ ቀድሞ እንቅፋት በማኖርና አልፎ ተርፎ ግባችንና ውጤታችን ላይ ገብቶ የሚጠብቀን፣ ለብዙ አደጋ እንድንጋለጥ - የሚጋብዝ፣ እግዚአብሔር ለሰዎች ከሰጠው ጤናማ ባሕርይ የወጣና የራቀ የዝሙት ጠባይ በማለማመድ፣ በማውረስ፣ በማዛባትና፣ በማሸነወር፣ ኑሯቸውንና ሕይወታቸውን በማርከስ፤ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሣደር የሚችል ክፉ መንፈስ ቢሆንም፣ ለኃያሉ አምላካችን ለእግዚአብሔር ከተገዛን፣ ሣይወድ በግዱ የሚንበረከክና የሚሸነፍ ጠላት ነው። ‹‹እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች እራሳቸሁን አዋርዱ፤ እርሱ ስለእናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት። በመጠን ኑሩ ንቁም፣ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደ አሚያገሳ አንበሳ ይዞራል። ›› 1ኛ ጴጥ.5÷6-8

## 1.3 የዝሙት መንፈስ

«የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው»
1ዮሐ. 3÷10

ለብዙ ዘመን ያህል የካበተ የማማለያ ልምድ ያለውና የሰዎችን መልካም ጠባይ የሚያበላሸው አንዱ የዝሙት መንፈስ ሲሆን፤ ዘወትር እንደ አዲስ ነገር አመልካች በመሆንና ግፊትን በማጠናከር፤ በልብ ውስጥ የሩካቤ ቅስቀሳ በማድረግና ሰዎች ዝሙትን፤ እንደተለመደ (ኖርማል) ነገር አድርገው እንዲወስዱና ድርጊቱን፤ በግልጽ ነውረኝነትና በድፍረት እንዲፈጽሙ ያነሳሳል።

የዝሙት መንፈስ፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው የተፈጥሮ ጠባይ በማዛነፍና በማዛባት፤ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፤ ሰዎችን በማስነወር፣ ለተፈጥሮ ግብር ተቃራኒ በማድረግና በማርከስ፤ ፍጹም የአመንዝራነትና የሴሰኝነትን ሰይጣናዊ ጠባይን ያወርሳል።

ዛሬ በዓለማችን ላይ ያለው የተራቀቀ ቴክኒዎሎጂ፤ በተለይም የኢንተርኔት አገልግሎት፤ ከሰጠው አዎንታዊ ጥቅም በተጨማሪ፤ በአሉታዊ መልኩ፤ ሰዎች በዝሙት፣ በኮከብ ቆጠራ፣ በሥነ-ልቦናና በፍልስፍና ወዘተ... መንፈሶች እንዲለከፉ፤ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል።

«እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፣ እነዚህም ዝሙትና ርኩሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጐምጀት ነው፤ በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል። » ቈላስይስ.3÷5-6





### የዝሙት መንፈስ የመግቢያ አቅጣጫዎች፤

ሀ. አብሮ በሚወለድ አጋንንት ዛር (በውርስ መንፈስ) በኩል!

ከሴትዋ ጋር አብሮ በሚወለድ ወንድ የአጋንንት ዛር፣ በተቃራኒው ደግሞ፤ ከወንዱ ጋር አብራ በምትወለድ ሴት የአጋንንት ዛር አማካኝነት፤

ለ. በመተት፤

ለዲያብሎስ ያደሩ ሰዎች ወደ ሌሎች አስመትተው በመላክ፤

ሐ. ከዓይን ላይ በሚነሣ መንፈስ (ቡዳ) አማካኝነት፤

ከውስጥ ወደ ውጭ በሚያይ የዝሙት መንፈስ ዓይን አማካኝነት የመንፈሱ ስሜት ይገባል።

መ. በማየት፣ በማዳመጥ፣ በማንበብ በኩል የሚገባ፤

የወሲብ ፊልሞችንና ስዕሎችን በማየት፤ ተመሣሣይ ወሲብ ነክ ንግግሮችን በሙሉ ስሜት በማዳመጥና ጽሁፎችን በማንበብ፤ በፊልሙ፤ በንግግሩና በጽሁፉ ላይ በሚኖር ሙሉ ተመስጦ ወይም ከፍተኛ ትኩረት የተነሣ፤ የዝሙት መንፈስ ወደ ሰዎች ይገባል።

ከዚሆ በተጨማሪ፤ መንፈሱ ከሰፈነበትና የሚውጠውን ለመፈለግ በሚንቀሳቀስበት አየርና መንገድ ላይ፤ ያገኛቸውን ሁሉ ይጠልፋል።

ለዚህ በተለይ ምሳሌ የሚሆኑን፤ በአገራችን በኑሮና በባህል ተጽዕኖ አስገዳጅት፤ ችግር የገጠማቸውን አንዳንድ እህቶቻችንን እያሳደደና፤ መጥፎ አማራጭ እያሳያቸው፤ የሴትኛ አዳሪነት ሕይወትን እንዲመሩ የመገፋፋቱ ጉዳይ ነው።

የእነዚህ የዝሙት መንፈሶች ተጋቦት ፈጣን በመሆኑ፤ ዲያቢሎስ ሰዎቹን፤ ቅብጥብጥ፣ እፍረተ-ቢስ፣ ነውረኛ፣ ርካታ-ቢስ ወዘተ... በማድረግ፤ በመጨረሻ ሥነ-ምግባራቸውና ግብራቸው፤ ለክርስቲያናዊ ሕይወት የሃይማኖት ቅድስና አደገኛ ይሆናል።

የሩካቤ ክፉ መንፈሶች ከሌሎቹ የጥፋት መንፈሶች ለየት ባለ መንገድ ብዙ ጠባይ አላቸው። ከነዚህም ውስጥ <u>ለምሳሌ፦</u> ሴት አጋንንት ዛር ከወንዱ ጋር አብራ ከተወለደች፤ በእድገቱና በዕድሉ ስለምትቀና ሩካቤውን ለራስዋ በምትፈልገው መልክ ትቆጣጠራለች። በዚህ የተነሳ ሰውየውን ዓይነ-አፋር፣ ፈሪ እና ድንጉጥ ልታደርገው ትችላለች። በሴቷ ውስጥም ያለው ወንድ አጋንንት እንደዚሁ ዓይነት ተመሣሣይ ጠባይ ያሳያል።

ብዙ ጊዜ ይህ የዝሙት መንፈስ በዛር በኩል ውርስ ሆኖ ሲመጣ፤ ወንዱንም ሆነ ሴቷን ፍጹም <u>ዓይን ወደ አወጣ ሴሰኝነት</u>፤ <u>በተቃራኒው</u> ደግሞ፤ ወደ <u>ዓይነ-አፋርነት</u> በመለወጥ ከፍተኛ አለመግባባት በባልና በሚስት መካከል በመፍጠር፤ የወንዱ ሕይወት በሴቷ፣ የሴቷ ሕይወት ደግሞ፤ በወንዱ እጅ እንዲያልፍ ሊያደርግ ሁሉ ይችላል።

ሌላው ደግሞ፤ ሁለቱንም ጾታዎች፤ ልባቸውን፤ የሩካቤ ስሜታቸውን የሞተ አድርጎ በማሳቀቅ፣ የሚያዝኑና የሚያለቅሱ ብቸኛ ሰው ሆነው፤ የሌሎችን ትዳርና ልጆች ሲያዩ እንዲማረሩ አድርጎ፤ ሕይወታቸውን በራሳቸው እጅ እንዲያሳልፉ፤ ይህ የዛር መንፈስ ግፊት ያደርጋል።

የመንፈሱ ተጽዕኖ እጅግ ከባድና የሰዎችን ጠባይ ወደ አውሬነት ሁሉ እስከመለወጥ ያደርሳል። ምክንያቱ ደግሞ፤ ተደጋግሞ እንደተገለጸው፤ አብሮ የተወለደው አጋንንት ዛር ሙሉ በሙሉ ከሰዎቹ ጋር ስለተዋሃደና ቤቱን በላያቸው ላይ ሠርቶ፤ ‹‹ዘሬ ናቸው›› እያለ ስለሚፎክር ነው።





## 1.4 <u>ከዓይን ላይ የሚነሣ መንፈስ</u>

## <u>(ቡዳ)</u>

ከዓይን ላይ የሚነሣ መንፈስ (ቡዳ) ሰዎችን የተለማመደ ለዘመናት ከሰው ልጆች ጠባይ ጋር ተመሳስሎ የኖረና ዘሩ ያደረገ፤ ዓይነቱ ይለያይ እንጂ፤ ሰውን በከፍተኛ ደረጃ የማጥቃት ልምድ ያካባተ፤ የቁጋ ይዞ፤ መቼ እንደሚጥል መረጃ ያለው፤ ከመተቶች ሁሉ በበለጠ ሁኔታ፤ የከፋ ጉዳት የሚያደርስ፤ ከአንዱ ወደ ሌላው ረቀቅ ባለ ችሎታ የሚተላለፍ አደገኛ የሆነ መንፈስ ነው። *(ከዓይን ላይ የሚነሣ መንፈስን ከዚህ በኋላ በአጭሩ፤ <u>ቡዳ</u> እያልን እንጠራዋለን።)*

### <u>የመንፈሱ የመግቢያ አቅጣጫዎች፤</u>

ሀ. <u>ከቤተሰብ የሚወረስ ዛር ፤</u>

ብዙ ጊዜ፤ የቡዳ መንፈስ መነሻው፤ ከእናት፣ ከአባት፣ ከአያት፣ ከቅድመ አያት ከቅም አያት ወዘተ... ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ዛር ሲሆን፤ በመዋለድ፤ በአካል፣ በደምና በነፍስ ውስጥ ተዋሕዶ፤ እየተወራረሰ እንደ ልክፍት የሚይዝ ነው።

ለ. <u>በሌሎች ላይ የሚያርፍ መንፈስ፤</u>

ይህ <u>ከመነሻው</u> ተሸጋጋሪ ሳይሆን፤ <u>ከውጪ ወደ ውስጥ</u>፤ በዓይን አማልጅነት ወደ ሌሎች የሚሄድና <u>በሌሎች ላይ የሚያርፍ መንፈስ</u> ሲሆን፤ በኋላም ተመልሶ፤ <u>ከውስጥ ወደ ውጭ ሌላውን ለመብላት</u> የሚንቀሳቀስ ጠላት ነው። ከሰባት ዓመት በኋላ ግን፤ ራሱ ቡዳው ተሻጋሪ መንፈስ ይሆናል።

መንፈሱ በሰውነታችን ውስጥ ሥፍራ የሚይዘው፤ እንደ ዓይነ-ጥላ መንፈስ ሁሉ <u>በሶስት ቦታዎች</u> ላይ ነው።

በመጨረሻም ይህ መንፈስ እየተሸጋገረ፤ በተለይ፤መልከ-መልካምና ቆንጆ የተባሉት ሰዎች ላይ ሁሉ እያረፈ፤ የማጥቃት አድማሱን የሚያሰፋ ነው።

‹‹ **እገሌን ወይም የእገሌን ልጅ ቡዳ በላው!›› ይባላል።** ጥያቄው ግን ማን በላው? እንዴት ተበላ? የሚለው ጉዳይ ነው። በዋናኝነት ይህ ተሸጋጋሪ የቡዳ መንፈስ እናት ወይም አባት ላይ ሊኖር ይችላል።

የተሸጋጋሪው መንፈስ አዚም ቤት ውስጥ እስካለ ድረስ፤ የቤተሰቡና የልጆቹ ዕድል ሁሉ፤ በአጥቂው መንፈስ ኃይል ሊወሰን ይችላል። በዚህ መሠረት በሚወለዱት ልጆች ላይ፤ግልጽ ጉዳትና እንከን በመፍጠር፤ አካላቸውና አእምሯቸው እንዲዛባ ያደርጋል።

ልጆች ያለ ቀድሞ ጠባያቸው፤ ውስጣቸው የተፈጠረው ክፋት፤ በአንድ ጊዜ ወደ ላይ እንዲወጣ ከሚያደርገው ምክንያት አንዱ፤ ይህ የተሸጋገረ፤ አሊያም ከሌሎች መጥቶና አርፎ እንደገና ወደ ቤተሰብ በሚሰራጨው የቡዳ መንፈስ ጠንካራ አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሣ ነው።

ማንኛውም ሰው፤ በቡዳም ይበላ፤ በመተትም ይታሰር፤ በአጋንንትም ይያዝ፤ በአስማተኞችም ይጠለፍ፤ በመስተ-ፋቅርም ይግባ፤ <u>ከሰባት ዓመት በኋላ</u> ግን፤ ያ ሰው ወደ ቡዳነት ይለወጣል። እናት ልጇን ምን ብትወድ እርሷ ላይ ባለው መንፈስ አማካኝነት፤ ልጇን ራስዋ ትበላለች። በሌላ አነጋገር፤ እርሷ ላይ ያለው መንፈስ ልጇን አጠቃው (በላው) ማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚገባው ይህ መንፈስ፤ የሌሎች ሰዎችን ባሕርይ ይዞ ስለሚመጣ፤ አንዳንድ ለየት ያሉ ጉዳቶችን ሲያስከትሉ እናያለን።

<u>ለምሳሌ</u> ለምጽ እና የቡዳ መንፈስ ያለባት ሴት፤ መንፈሱ፤ ያንን ለምጽ የፈጠረባትን ችሎታና ኃይል ያወቀና የተረዳ ስለሆነ፤ ሌላ ሰው ላይ ሄዶ በሚያርፍበት ጊዜ፤ ለምጹን እዚያ ሰው ላይ ያሳያል።





በሌላ አገላለጽ ፤ በመንፈሱ የውጊያ ሥልትና ጥቃት መሠረት፤ በበይው ላይ ያለው ለምጽ፤ በተበይው ላይ ይታያል፤ ይወጣል ማለት ነው።

ሰውየውን የበላው መንፈስ እጅግ በጣም ጅል ከሆነ ደግሞ፤ በቡዳ የተበላው ሰው፤ የቀድሞው የራሱ ባሕሪይ ይጠፋና፤ ፍጹም ጅልና አዚም የተጫነው ይሆናል። በዚህ ጊዜ ለተወሰነ ወቅት፤ ግራ መጋባት፤ ተስፋ መቁረጥ፤ መናደድ፤ በሕይወትና በኑሮ ውስጥ አዚም እስኪጫነው ድረስ መቅበጥበጥ፤ አለመመቸት ወዘተ... የሚታይበት ሲሆን፤ ሰባት ዓመት ከሞላው በኋላ ደግሞ፤ ይህንኑ መንፈስ ለልጆቹ ሲያካፍልና ሲያስተላልፍ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ዘካሪያስ፤ « **የሰው ጠላቱ ቤተሰቡ ይሆናል** » በማለት የሚገልጸው፤ አንድም፤ ይህንን የውርስ ክፉ መንፈስ ጠባይን ለማመልከት ነው።

እንዲህ ዓይነቱን መከራ በክፉው መንፈስ አማካኝነት ዩወረሱ ሰዎች፤ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ የሚከተሉት ጠባያት ይታይባቸዋል።

- ለመንፈሳዊ ነገር የሚሰጡት ግምት በዜሮ የተባዛ ነው። ለሥራ የሚሰጡት ትኩረት፤ ጸሎት ከማድረስ የላቀ ነው። ስለ ቅድስናና ሰማያዊ ነገር ሲነገራቸው ወዲያውኑ የተቃውሞ ድምጽ ያሰማሉ። ሌላው ደግሞ ቅዱስ ወንጌል በሚነገርት ጊዜ፤ ለራሳቸው የሚመቻቸውን ብቻ መርጠው ይሰማሉ። ነቅሰው የሚያስቀሯቸው ቃላቶች ይበዛሉ። **<u>ቅዱስ ቁርባን</u>** ትልቅ ሥርየት እንደሆነ፤ ዲያብሎስን እንደሚቃወም፤ **<u>የዘር መንፈስን እንደሚያቆም</u>**፤ ወደ በረከት እንደሚመራ፤ የሰማያዊ መንግስት ልብስ እንደሆነ ሲነገራቸው ይቃወማሉ፤ ገና ውስጤ አልተቀበለውም ይላሉ።
- የሌሎችን ምክር አይሰሙም፤ በራሳቸው መንገድ ብቻ ይመራሉ። እነኚህን በመሳሰሉ ሁኔታዎች ውስጥ ኖረው፤ የልጆቻቸውን የጉዞ አቅጣጫ ዞር ብለው ሲመለከቱ ደግሞ፤

## <u>ሴቶችን አለባል የሚያስቀሩ የዛር፣ የዓይነ-ጥላና የቡዳ መንፈሶች፤ አንዱ የጋራ ጠባይ</u>

ባለፉት ርዕሶች ውስጥ በስፋት እንደተጠቀሰው፤ ብዙ የዛር፣ የዓይነ-ጥላና የቡዳ መንፈሶች ከሚያደርሱት ተመሣሣይ ጥቃቶች መከካል አንዱ፤ ቆንጆና ውብ የሆኑ ሴቶችን ቀድሞ በመያዝ፤ ያለ ትዳርና ያለ ልጅ በማስቀረት ዕድሜያቸውን በብቸኝነት እንዲያልፍና ስለ ትዳር ግምት እንዳይሰጡ በማድረግ የሚያጠቃቸው ሲሆን፣ የሚጠጉዋቸውንም ወንዶች በመቀጣት፣ በመናቅ፣ በማቃለል፣ በመምረጥና ቈንጥ በማውጣት ወሬ እየተዋጋ፤ የጋብቻና የመውለድ ዘመናቸው እንዲያልፍባቸው ያደርጋል።

ይህም የዘመናችን ሴቶች አንዱ ትልቅ ችግር ነው። <u>ባል ከልክል መንፈስ</u> ከሌላው ለየት የሚያደርገው፤

- ውብ ሴትን ለትዳር የሚጠይቋት ወንዶች ከሚገጥማቸው ችግሮች መካከል፤ መፍራትና መደንገጥ ዋናው ሲሆን፤ በጣም ከደፈሩ ደግሞ፤ መንፈሱ በስውር በመምታት፤ ራስ ምታት፣ የሩካቤ ኃይልና ከልብ ውስጥ ፍቅር ማጣት፣ መጨነቅና መቅበጥበጥ ከብዙዎቹ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፤
- የልጅቱን የአካል ጠረን፤ ከትንፋሽ ጀምሮ እስከ አካል ወዝ ድረስ፤ ወደ መጥፎ ሽታ ይለውጠዋል፤ ይህም ጠረን በሽቶ የማይጠፋ ዓይነት ሆኖ፤ ጠያቂውን ወንድ ያባርረዋል፤
- የልጅቱን ጠባይ በመለወጥ፤ ቁጣ፣ ግንባረ ደረቅ፣ ኩስታራ፣ የሚያቃጥል ፊት፣ የምትናገረውንም ቃልና ሐሳብ መራራ፤ ድምጽዋንም አስፈሪ በማድረግ፤ የጋብቻን ሕይወት ይከለክላታል፤
- ልጅቱን ለትዳር የሚጠይቃት ወንድ እንዳይኖር፤ መልኳንና ውበቷን በመለዋወጥ፤ ማድያት፣ የፊት ጠባሳ፣ ቡጉር፣ የአካል ማበጥ፣ ራስ ምታት፣ የሰውነት ፎረፎርና የፊት





መጣመም ወዘተ… የመሳሰሉትን ችግሮች በማምጣት፤ ተስፋ ያስቆርጣታል፤

- በግንኙነት ወቅትም፤ የማሕፀን መጥበብና የሕመም ችግር በመፍጠር፤ ጋብቻው እንዲቀር ወይም እንዲፈርስ ከማድረጉም በላይ፤ በብቸኝነት ሆድ በማስባስ እያስለቀሰ ዓይንን የማጥፋት ጉዳት የማድረስ ችሎታም አለው። እንደዚህ ዓይነት የመንፈስ ጥቃት በሕክምና ዘዴ፣ በሳይኮሎጂ፣ በሰው ሰራሽ ሙያና ጥበብ አይፈታም።

እነኚህ ጥቃቶች ሁሉ፤ ዛሩ ለዘመናት ሲገበር ከመኖሩ ጋር ተያይዞ፤ የሚመጡና የሚፈጠሩ ችግሮች ናቸው።

ጤናን ማወክ ሽንል፤ <u>ለምሳሌ፣</u> ዓይኗ ቆንጆ ከሆነ፤ ዓይኗን ማቃላት፣ ማሞጭሞጭ፤ ማጥፋት፣ ጥርት ያለ ገላና ፊት ካለት፤ ማጥቆር፣ ማዲያት ማልበስ፣ ማኰጎርጎር፣ ማበላሸት፤ ውበቷን ማርገፍ፣ ጸጉሯ የሚያምር ከሆነ ደግሞ፤ ተነቅሎ እንዲያልቅ፣ ፎሮፎር እንዲነሰነስበትና ተባይ እንዲወረት ወዘተ… ያደርጋል።

መንፈሱ በአብዛኛው በዚህ መልኩ፤ ለሰው ልጆች ሕይወት ምንም ዓይነት መረጃ ሳይሰጥ፤ ውስጥ ለውስጥ አድፍጦና ተደብቆ በመቀመጥ ከቆየ በኋላ፤ በአካል ላይ በግልጽ የሚታይ ጉዳት ያስከትላል።

## የአብ'ርና አንክርት መንፈስ

በዘመናችን ከፍተኛውን ቦታ ከያዙ የርኩስ መንፈስ ጥቃቶች መካከል፤ <u>አብረውና አንክራተው</u> ተብሎ የሚላከው የድግምት መንፈስ አንዱ ነው። ይህ የአንክርት መንፈስ በብዛት የሚላክበት መንገድ፤ በወፍ፣ በአሞራና በሰጎን እንቁላል፣ በጅብ እግርና በጎሽ ሾኽና፣ በፍልፈል፣ በአይጥ፣ በሽኮኮ፣ ነጋዴ በነበረ ሰው የመቃብር አፈር፣ እንዲሁም ረጅም አገር በሚሄድ የወንዝ ውኃ ወዘተ... ላይ በመድገም ነው።

አሠራሩና ክንውኑም፤ የተደገመበትን የወንዝ ውኃና የመቃብር አፈር በሩ ላይ በመርጨትና በመበተን፣ አስሮ በመጣል፣ አይጥ፣ ወፍና አሞራ ወዘተ... ገንዘ በማስቀመጥ፣ ወይም ቆፍሮ በመቅበር ሲሆን፣ መንፈሱ የተሰጠውን የግብር ዓይነት ተቀብሎ ወደ ሰውየው ወይም ወደ ሴቷ በስማቸው ይላካል።

**<u>የአብርና የአንክርት መንፈስ ምልክቶች፤</u>**

- ተመቻችቶ ከሚኖርበት አገር፣ ወይም መንደር ሳይታሰብ ድንገት በመነሳት፤ ከዘመዶቹ ርቆ፤ <u>ቤተሰቡንና ንብረቱን ጥሎ</u> ወደ ማያውቀው አገር እልም ብሎ ወጥቶ መሄድ፤
- ድንገት ያለውን ሃብት <u>በርካሽ ዋጋ ሸጦና በትኖ፤</u> ብር ብሎ ወደ ማያውቀው አገር መጓዝ፤
- ወገን፣ ቤተሰብ፣ ልጅ፣ ሚስት እዚህ ቀረኝ ሳይል፤ ያለ ዕቅድና ዝግጅት፤ እግሩና ገንዘቡ ወደ ወሰደው አቅጣጫ ተሳፍሮ መሄድ፤
- በየሄደበት ቤተሰብ እየመሠረተ መኖር፤ መንፈሱ ሲነሳበት ወይም ሲያስገድደው ደግሞ፤ ያንን አካባቢ ለቆ መጥፋት፤ በሌላ አነጋገር፤ በየጊዜው አዳዲስ ኑሮ እንዲጀምር ማድረግ፤ እንደገና ሠርቶ መቋቋም ሲጀምር፤ ዳግመኛ ሁሉንም ትቶ በሮ እንዲጠፋ መንፈሱ ያነሳሳዋል፤





- ሕሊናው እስኪነቃ ድረስ፣ አገር አቋርጦና ድንበር ተሻግሮ ብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች እንዲጓዝ ማድረግ፣ በጉዞውም ማሰላቸትና ተስፋ ማስቆረጥ፤
- የመጀመሪያውን ቀዬ ለምን ለቆ እንደሚሄድ እንኳን ሳያውቅ፤ በረሃ ለበረሃ፣ ወንዝ ለወንዝ፣ አገር ለአገር እያቋረጠ ሲጓዝ ኖሮ፤ እንደገና መመለስ፤ በሕብረተሰቡና በአካባቢው ሰዎች ዘንድ፤ <u>ሲበርድለት ዞሮ መጣ</u> በመባል የሚነገርለት፤ ራሱ ግለሰቡ ሲጠየቅ፤ የአዙሪት አመሌ ተነስቶብኝ፤ ስዞር ኖሬ መጣሁ በማለት፤ ሰቆቃውን የሚናዘዝ፤

በሌላ በኩል ደግሞ፤ <u>አገሩንና መነሻውንም በመርሳት፤ ዳግመኛ ሳይመለስ</u>፤ ዕድሜ ልኩን እየተጓዘ በሰው አገርና በረሃ ላይ ወድቆ እንዲቀር፣ በአውሬ እንዲበላ፣ በሰው እጅና በአደጋ እንዲሞት፣ ወጥቶ በሮና ተንከራቶ የሕይወት ዘመኑ መንገድ ላይ እንዲያበቃና እንዲዘጋ ማድረግ፤ የዚህ <u>የአብርና አንክርት መንፈስ</u> ዋንኛ መለያና ትልዕኮው ነው።

## በሰውነት ውስጥ የመናፍስቱ መሸኮት

አንዳንድ ሰዎች በሕይወታቸው፣ በአእምሮዋቸው ወይም በሐሊናቸው እና በልቦናቸው ውስጥ፤ ቅጥ ያጣ ሽኩቻ ሲካሄድ ይሰማሉ:: ከዚህም የተነሳ ድንገት ማንም ሳይጠራቸው «አቤት! ወይም እመት» በማለት ይነሳሉ:: ወይም <u>ለምን ተጠራሁ?</u> ብለው ይጠይቃሉ:: በዚህ ጊዜ የሚጠራቸው አካል ወይም የሚያዳምጡት ጥሪ፤ ከውጭ ሌላ ሰው ይመስላቸዋል::

ይህ ሁኔታ ሲደጋገም ግራ በማጋባት ሕልውናቸው ይፈተናል:: በመጨረሻም፤ የዛር፣ የውቃቢ፣ የጨሌ፣ የዓይነ ጥላ፣ የቡዳ ወዘተ... መንፈሶች የጋራ የተጠናከረ የከፉ ጥቃቶች አብረው ሲዘነዘሩና መንፈሱ መቶ በመቶ <u>በተደጋጋሚ እየተጣራ</u> ግለሰቦችን በሚያስጨንቅ ሁኔታ በስፋት ሲቆጣጠራቸው፤ የአእምሮ ሕሙማን ሆስፒታሎች ሕክምና የማያድኑትና የማይመልሱት እብደት ላይ ይወድቃሉ::

ምክንያቱም፤ ጥሪው በተደጋጋሚ የሚቀርበው ከዲያብሎስ ስለሆነ ነው::

ከዚህ በኋላ ለረጅም ዘመን ቆሻሻ ላይ እየተኙ፤ ያገኙትንም እየበሉ የሚኖሩ ሲሆን፤ ጀርም፣ ቫይረስና ባክቴሪያ የተባሉ ተህዋሲያን ሁሉ ጤናቸውን አይጎዱም::

ምክንያቱም ዲያብሎስ የሰው መንገላታትና መውደቅ የሚያረካው ስለሆነና መንፈሱ ራሱ ሁሉንም ዓይነት ተህዋሲያን የሚወክል በመሆኑ፤ ለረጅም ዘመን የወደቀና የተጣለ ቆሻሻ እያበላው ሊያኖረው ይችላል:: ይህም የዚህ ክፉ መንፈስ አንዱ ምልክት ነው::

«ዲብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራል»
1ኛጴጥ5÷9





## 1.5 <u>የግፍ መስተ-ፋቅር መንፈስ</u>

«የሰይጣንንም ጥልቅ ነገር» ራእይ 2÷24

የመስተፋቅር መንፈስ <u>ሕሊናና ልቦና ውስጥ ገብቶ</u> ማሳሰብ፤ ማስተከዝ፣ ማስጨነቅ፣ መናፈቅ፣ ሀሳብን ማብዛትና ማጠናከር፣ መገፋፋት፣ የተፈለገውን ወንድም ይሁን ሴት በሃሣብ በማሳየት፤ እንቅልፍ፣ ምኞትና ዕረፍት ማሳጣት፤ በመጨረሻም መንፈሱ ራሱ እየመራ ወስዶ ሰይጣኑን ካስላከው ሰው ጋር የሚያገናኝ፤ የዲያብሎስ ልዩ የዘመቻ ምሪት ነው:: ብዙ ሰዎች መስተ-ፋቅርን የሰይጣን ሥራ ነው ብለው አይገምቱም:: እምነታቸውና የሚሰጡት ግምትም ከጥልቅ ችሎታ፤ ከትምህርት ከጥናትና ምርምር የመነጨና የተገኘ ጥበብ ነው በማለት ነው::

ሐቁ ግን፤ <u>መስተ-ፋቅር ከሰይጣን ጥልቅና ውስብስብ ሥራዎች</u> መካከል አንዱ መሆኑ ነው:: የመስተ-ፋቅር መንፈስ የአገባብ ሥልት ይለያይ እንጂ፤ ጥቃቱ አንድ ዓይነት ነው:: በውጭው ዓለም ይህንን መንፈስ እንደ ዕድገት፤ ሀብት፤ እውቀት ወዘተ... ተቆጥሮ እሠራሩን የሚማሩ ብዙ ገንዘብ አፍሰው ይህንኑ የሚሮት መንፈስ ሲጠቀሙ የሚታዩ በርካቶች ናቸው::

- <u>በአብዛኛው መንፈሱ የሚላክባቸው ሰዎች፤</u>

ቆንጆ የሚባሉ መልከ-ቀና፤ መልከ-መልካም፤ ማራኪ የሰውነት አቋም ያላቸው አካላዊ ግርማ ሞገስን የተላበሱ፣ በሀብትና በገንዘብ፣ በትምህርቱ፣ ብችሎታ፣ በሥልጣንና በማዕረግ ወዘተ... ከፍ ያሉትን ሰዎች ነው:: መንፈሱ በብዙ መልክና መንገዶች ወደ ሌሎች ሰዎች የሚላክ ሲሆን በአብዛኛው የተለመደው የመስተፋቅር አሰራር ግን በሁለት ዋና ዋና አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ ነው::

እነርሱም <u>በፍቅርና በጋብቻ ግንኙነት ላይ</u> እንዲሁም፤ <u>ከገንዘብና ከንብረት</u> ጋር የተያያዙ ናቸው:: «የልጆችን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም» ማቴ. 15÷26

ማንጸባረቅ ይጀምራል። ከዚያ በኋላ ማጣላት፤ መጋጨት፤ አለመግባባት፤ ትዳርን እስከማፍረስ ድረስ የሚዘልቅ ከባድ ግጭትና ሁከት ቦታ ይይዛል።

ሌላው አደገኛ ነገር፤ ሰይጣን ከዳራቸው ሁለቱ ሰዎች የሚወለዱት ልጆች ጉዳይ ነው። ከጽንስ ጀምሮ ዲያብሎስ ልጆቹን እንደልክፍት ይዞ፤ በአእምሮና በአካል የተጎዱ ሆነው እንዲወለዱ ያደርጋል። በመሆኑም መስተ-ፋቅር ማለት፤ ከሰይጣን ጋር መፋቀርና የተጣለውን ክፉ መንፈስ ማግባት ማለት ነው።

<u>ሌላ ምሳሌ እንመልከት፤</u>

አንዳንድ ሰዎች ለትምህርት፤ ለሥራና ለተለያየ ጉዳይ፤ ከትዳርና ከፍቅር ጓደኞቻቸው ረዘም ላሉ ጊዜያት ሲለዩ፤ ሚስታቸው ከሌላ ወንድ፤ ባላቸው ደግሞ ከሌላ ሴት ጋር እንዳይባልጉ ለማድረግ፤ <u>ጠባቂ የመስተ-ፋቅር መንፈስ</u> ያስልካሉ።

በትክክል መንፈሱ ሁለቱም እንዳይማግጡ፤ የፍትወት ስሜታቸውን አቀዝቅዞና ከልሎ ይጠብቃቸዋል። ሌላ ሰው እንዳይመለከታቸውም፤ የተመለከታቸውን ሰው ፍላጎት በመንፈሱ ኃይል በማገድ ይከለክለዋል።

መንፈሱ ይህን የሚያደርገው ለላከው ሰው አስቦ ሳይሆን፤ ሰዎቹን የራሱ ለማድረግ ነው። ይህም፤ አንዴ ሰይጣኑ ወደ እነርሱ ከገባ በኋላ፤ ጠባቂው መንፈስ፤ <u>ሴቷን እንደሚስቱ፤ ጠባቂዋ ሴት መንፈስ ደግሞ፤ ወንዱን እንደ ባል የራሱ / የራሷ</u> አድርገው ስለሚይዙ ነው። በመጨረሻም፤ አገር ለቀው የተጓዙበት ትምህርትና ሥራ ተጠናቆ ባልና ሚስቱ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፤ ጨርሶ መግባባትና ሰላም ያጣሉ። ምክንያቱም በዚህ መጽሐፍ ልዩ ልዩ ርዕሶች ላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው፤ ሁለቱም ሰዎች በውስጣቸው ዲያብሎስ በመስተ-ፋቅር ያጋባቸው <u>ሌላ የክፉ መንፈስ ባልና ሚስት</u> ስላሉዋቸው ነው።





ሰዎችን ጨምሮ ሌሎች እንስሳትና እጽዋት፤ የእግዚአብሔር ጥበቃ አላቸው። የሰይጣን ጥበቃ ውጤቱ ግን፤ ከላይ በመስተ-ፋቅር እንደተገለጸው አስከፊ ነው። **‹‹እግዚአብሔር የሚወድዱትን ሁሉ ይጠብቃል›› መዝ:144 (145) ÷20**

<u>ስስተኛ ምሳሌ እንመልከት፤</u>

የሚያስቀና ትዳር ያላቸውን ባልና ሚስት ለመበጥበጥ፣ ለማለያየት ብሎም ለማጋደል፤ አንድ ሴት የሌላዋን ሰው ባል <u>በመስተ-ፋቅር መንፈስ</u> ትጠልፈዋለች። በዚህም ሰውየው እርሷን እንዲወድ፣ ሚስቱን እንዲጠላ፣ ስለእርሷ ብቻ እንዲያስብና እንዲያወራ፣ ከእርሷ ጋር ብቻ ግንኙነት እንዲፈጽም ወዘተ... በማድረግ፤ ግለሰቡ <u>በተለይ ከሚስቱ ጋር በሚሆንበት ሰዓት</u>፤ የጨዋታው መክፈቻና የንግግሩ መጀመሪያ ሁሉ፤ መንፈሱን ስለላከችበት ሴት ይሆንና፣ የእርሷን ውበት፣ሙያ፣ችሎታ፣ እውቀት፣ ቁንጅና፣ ጥሩ ሰውነት፣ ታላቅነት ወዘተ... <u>መናገርና መመስከር ብሎም፤ ከእርሷ ጋር አብሮ መዋልና ማደር</u> ይጀምራል።

ሴቷንም፤ ትዳሯን ለመረበሽና ኑሮዋን ለማበላሸት፤ እንደዚሁ ዓይነት ተመሣሣይ <u>የመስተ-ፋቅር መንፈስ</u> ይላክባታል። ከዚህ በኋላ፤ ሚስት ባሌ ሌላ ሴት ወደደ፤ ባል ደግሞ በበኩሉ ሚስቴ ሌላ ሰው አፈቀረች በማለት፤ <u>ሕይወት እስከማጥፋት ድረስ የሚዘልቅ አምባጓሮ</u> ይቀሰቀሳል። ዛሬ ብዙ ሰዎች እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚፈጠረው፤ በክፉው መንፈስ ግፊት መሆኑን ገና አልተረዱም። ከእነዚህ የሚያስቀና ትዳር ከነበራቸው ባልና ሚስት በስተጀርባ ያለው <u>ጠላት</u> ግን፤ <u>ዲያብሎስ</u> ነው።

<u>ሌላ ምሳሌ</u>፦ በአጋጣሚ አንድ ሰው፤ <u>ከዚህ በፊት የሚያውቃት ሴት ወይም የማያውቃት ልትሆን ትችላለች</u>፤ በድንገት መንገድ ላይ አግኝቷት ሰላምታ ከተለዋወጠና ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል አብሯት ቆይቶ፤ ተለያየ እንበል።

ይህ ከሆነ ቀናት በኋላ ወይም ወድያውኑ፤ ሰውየው ስለሴትየዋ ወይም ስለ ልጅቱ ማሰብ ይጀምራል። ራሱ እስኪገርመው ድረስ፤ ሌላ ሰው ለመጥራት ሲፈልግ፤ የዚያችን ልጅ ስም ሊጠራ ሁሉ ይችላል። ጉዳዩ በዚህ ሳያበቃ፤ ይባስ ብሎ ሌት ተኝቶ በሕልሙ ከልጅቷ ጋር ሲዳራ ሁሉ ሊያይ ይችላል።

ይህ ሊሆን የሚችለው፤ በሴትዮዋ ውስጥ ያለው ከዓይን ላይ የተነሣው ( ቡዳ ) የመስተ-ፋቅሩ መንገደኛ መንፈስ፤ ከውስጥ ወደ ውጭ በፍጥነት ተንቀሳቀሶ፤ ወደ ሰውየው ውስጥ ዘሎ በመግባቱ ነው። ሁኔታው፤ የአጋንንቶቹን ኅብረትና ፈጣን የጥቃት እንቅስቃሴ የሚያመለክት ነው። እንደዚህ በፍጥነት የሚገቡ መንፈሶች፤ ምልክታቸውን በገቡበት ፍጥነት ወድያውኑ፤ ወይም በጥቂት ቀናት ውስጥ አሳይተውና ግራ አጋብተው፤ ጨርሰው ሲወጡ አሊያም ደግሞ፤ አመቺ ሁኔታ ከገጠማቸው፤ በኃጢአት ኑሮ መርዘው ሊቆዩና ሊኖሩ ይችላሉ።

## የመስተ-ፋቅር ገንዘብና ንብረት፤

በዚህም ሄድን በዚያ፤ በዚያም መጣን በዚህ፤ ዛሬ ዓለምንና ሰውን ሁሉ የሚያምሰው ሰይጣንና ገንዘብ ነው። ለጊዜያዊ ጥቅም ሲባል ብቻ፤ ገንዘብን ያለ አግባብ ለማግኘት ከእግዚአብሔር መንገድ ወጥተው በዲያብሎስ እጅ ውስጥ በመግባት፤ የጭንቅ ኑሮ የሚኖሩና ተስፋ የቆረጡ ብዙዎች ናቸው።

በክርስቶስ ኃይል የፈረሰው የዲያብሎስ አሠራር በእኛ አኗኗርና ምግባር ተመልሶ ተገንብቷል።‹‹የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ **የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ** ።›› ከዚህ የጠላት አሠራር መካከል፤ አንድ ሰው ያለውን ገንዘብና ንብረት እያነሳ በክፉ መናፍስት አስገዳጅነት ለሌላ ሰው እንዲሰጥ የሚያደርገው የመስተ-ፋቅር መንፈስ ነው።





በዚህ በኩል ያለውን የመንፈሱ ሥልትና አሠራር በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን።

### ሀ. ያለንን ገንዘብና ንብረት እያወጣን መስጠት፤

በዚህ አቅጣጫ የሚላከው የመስተ-ፋቅር መንፈስ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው፤ ቤትም ሆነ ባንክ ቤት ያስቀመጥነውን ገንዘብና ንብረት፤ በመንፈሱ ኃይል እያወጣንና እንዳንሳሳትም በጥንቃቄ እየቆጠርን፤ ሰይጣኑን ለላከብን ሰው እንድንሰጥ የሚያደርግ መንፈስ ነው። በዚህ መንገድ ብዙ ሰዎች በመንፈሱ ልቦናቸውና ሕሊናቸው ታውሮ፤ ያላቸውን አራግፈው ለሌሎች ሰጥተዋል። በዚህም የተነሣ የበርካቶች ኑሮ ተናግቷል፤ ጎጆ ፈርሷል፤ ልጆች ተበትነዋል።

በዚህ በሰለጠነው ዘመንም፤ ከገጠር እስከ ዋናው ከተማ ድረስ በሜርኩሪ ፈሳሽ አማካኝነት ገንዘባቸውን የተዘረፉ ብዙ ሲሆኑ፤ የውሸት ብርና ዶላር በማሳየት ገንዘባቸውን ለአስማተኞች በማስረከብ፤ ራሳቸውን ስተው ቤት ውስጥ የቀሩ፤ ጥቂቶች አይደሉም።

እዚህ ላይ ግልጽ መሆን የሚገባው ነገር መንፈሱ የተላከበት ሰው ገንዘቡን ለሌላ ለማንም ሰው ሰጥቶ አይበትንም። የሚሰጠው በመስተ-ፋቅር ላሰረው፤ ማለትም ሰይጣኑን ለላከበት ሰው ብቻ ነው።

የመንፈሱ ሰለባ ቤቱ ያለው ገንዘብና ንብረት ቢያልቅበት እንኳን፤ ከሌላ ቦታ ሰርቆም ቢሆን እየመጣ፤ ለዚሁ በሰይጣን ለአሰረው ሰው ይሰጣል። ምክንያቱም ለዚያ ሰው ገንዘብ ካልሰጠ፤ በእርሱ ውስጥ የገባው መንፈስ ስለሚቆጣና ሕመም ስለሚልክበት ነው።

### ለ. የአሠሪነት የግፍ መስተ-ፋቅር፤

ሌላው የዚህ መንፈስ አስገዳጅ አሠራር፤ ሰዎች ለፍተው፤ ደክመውና ጥረው ያፈሩትን ገንዘብ በመስተ-ፋቅር ተጠልፈው፤ መንፈሱን ለላኩባቸው ሰዎች፤ ካሉበት ሩቅ ቦታ ወይም አገር ሆነው፤ ለራሳቸው አምስት ሳንቲም ሳያስቀሩ የመላካቸው ጉዳይ ነው።

የዚህ ምክንያቱ ደግሞ፤ በሕሊናቸውና በልቦናቸው ውስጥ የተቀመጠው መንፈስ የሚያዘው፤ ሠርቶ ገንዘብ መላክንና መስጠትን ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ ይህ አሠርቶ የሚያስልክና የሚያሰጥ መስተ-ፋቅር ይባላል፡፡

እነዚህ ምስኪን ዜጎች ውስጣቸው በገባው ርኩስ መንፈስ ኃይል አስገዳጅነት፤ ገንዘባቸውን ከአሠሪዎቻቸውና ከአለቆቻቸው እየተቀበሉ መላካቸውን አያውቁትም፡፡ ምክንያቱም፤ መንፈሱ ሕሊናቸውንና ልቦናቸውን ስለሰወረው ነው፡፡

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን፤ እንጀራ ፈልገው ወደ አረብ አገር የሄዱትና የተሰደዱት ሴቶች እህቶቻችን ናቸው፡፡ የሠሯትን በየጊዜው እየሰበሰቡ በክፉ መንፈስ ለሸበባቸው ሰው ልከው፤ መጨረሻ ወደ አገር ቤት ተመልሰው፤ ገንዘባቸውን ተበልተው፤ አመድ ላይ የወደቁና ራሳቸውን ያጠፉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡

ብዙዎች በዚህ መንፈስ የድካማቸውንና የላባቸውን ውጤት በመታለል፤ ተዘርፈዋል፤ ተቀምተዋል፤ ተክደዋል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የእግዚአብሔር አይደሉም፡፡ «የሰይጣንንም ጥልቅ ነገር» እንጂ! ራእ 2÷24

እንዲህ ዓይነት የጭካኔ ብትር ያረፈባቸው ወገኖች፤ ወደ ልቦናቸው ተመልሰው ስለላኩት ገንዘብ ሲጠይቁ፤ እንደሌለ ይነገራቸዋል፡፡

ወደ ፖሊስና ፍርድ ቤት ሄደው ሌላ ጣጣ እንዳያመጡም፤ መንፈሱን የላኩት ሰዎች፤ ርህራሄ በሌለው አስተሳሰብ፤ ጨርሶ ሊያጠፋና ሊገድል የሚችል ሌላ አዲስ ርኩስ መንፈስ፤ በእነዚያ የመከራ ሰዎች ላይ ይልካሉ፡፡ የዚህ ሁሉ ጭካኔ መሠረቱ ደግሞ፤ የተጣለውና የቀደመው ጠላት ዲያብሎስ ነው፡፡





ሐ. <u>ገሃዳዊ አሰጪ የግፍ መስተ-ፋቅር መንፈሶች፤</u>

ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ የመስተ-ፋቅር መንፈሶች፤ ለአንድ ለታወቀና ለሚፈለግ ግለሰብ የሚላኩ ሲሆን፤ ይህ ሶስተኛው መንፈስ ግን፤ ሀብት፣ ገንዘብ፣ ትምህርት፣ ሥልጣን፣ ማዕረግ ወዘተ... ያላቸውን የሚታወቁም ይሁን የማይታወቁ ሰዎችን ለማጥመድ ተብሎ፤ አጥማጁ ግለሰብ ገሃዳዊ አሰጪ የመስተ-ፋቅር መንፈሱን፤ <u>በራሱ ላይ አሠርቶ</u>፤ ከሰይጣኑ ጋር ቤተሰብ ሆኖ ይቀራኛል፡፡

ሌሎች ሰዎች ያላቸውን ገንዘብ፤ ጌጣጌጥ (ወርቅ፣ አልማዝ፣ ዕንቁ ሊሆን ይችላል) ሰዓት፣ መነጽር፤ የሞባይል ስልክ ወዘተ... <u>መንፈሱን</u> በራሱ ላይ ያሠራው ሰው ድግምት አድርጎ፤ ማለትም፤ ሰይጣኑን ጠርቶና ጎትቶ ሲነካቸው፣ ሲዳብሳቸው፣ ሲያነጋግራቸው፣ ሲጨብጣቸው፣ ሲስማቸው፣ ወዘተ... አጥቂው መንፈስ በፍጥነት ወደ ውስጣቸው ይገባና ወዲያውኑ ሕሊናቸውን በመሰውርና በማፍዘዝ፤ ያላቸውን ሁሉ ከቦርሳቸው እያወጡና፤ ጆሯቸው፣ እጃቸውና አንገታቸው ላይ ያለውን ጌጣጌጥ በሙሉ አንድ ሳይቀር፤ ሳይታወቃቸው እያወለቁ እንዲሰጡ የሚያደርግ <u>አስገዳጅ መንፈስ</u> ነው፡፡

የነካቸው ሰው ሳያስገድዳቸው፤ <u>«ቆይ አትሂድ»</u> እያሉ፤ ቦርሳቸውን እየበረበሩ ያላቸውን ሁሉ አራግፈው ከሰጡ ሁለትና ሶስት ሰዓት ማለትም፤ በመስተ-ፋቅሩ መንፈስ የዘረፋቸው ሰው <u>ደብዛውን ካጠፋና ከተሰወረ በኋላ ሲነቁ</u>፤ እጃቸው ላይ ምንም የቀረ ነገር እንደሌለ ይረዳሉ፡፡ ይህ ገሃዳዊ አሰጪ የመስተ-ፋቅር መንፈስ ይባላል፡፡

## የመንፈሱን ጥቃት በተለይ በልጆች ላይ አለመገንዘብ፤

የመስተ-ፋቅር መንፈስን ጥቃት ብዙ ሰዎች በተለይም አንዳንድ ወላጆች አይገነዘቡትም። ልጆች በት/ቤት፤ በኳስ ሜዳ፤ በፊልም ቤት በመኖሪያ አካባቢ ወዘተ... በሚውሉበትና በሚገኙበት አጋጣሚ ሁሉ፤ ሌሎች ሰዎች በሚልኩት የመስተ-ፋቅር መንፈስ ተጠልፈው ሊወድቁ እንደሚችሉ አይረዱም።

ልጆቻችን ከት/ቤት ሲፈናቀሉ፤ ትምህርታቸውን ሲያቋርጡና ከተለመደው የቀድሞ ጠባያቸው የተለየ አዲስ ደባል የሆነና ወጣ ያለ አመል ሲያመጡ፤ የመናፍስቱ ጥቃት መሆኑን ሳናውቀውና ሳይገባን ይቀርና ልጆቻችን ባለጉ ብለን በማግለል፤ ከቤተሰባዊው በረከት በጥጋብ እንደራቁ አድርገን እንወስዳለን። በዚህ የተነሳ ልጆቹ፤ ተጠልተው፤ ተወግዘው፤ ተሰድበውና ተረግመው መንገድ ዳር እንዲቀሩና ያለጊዜያቸውና ያለዕድሜያቸው ተቀጥፈው እንዲቀሩ እንጋብዛቸዋለን።

## መብትንና አማራጭን የሚያሳጣው የመስተ-ፋቅር መንፈስ አሠራርና አደጋው

ይህ ፍቅርን፣ የባለቤትነት ሕልውናንና መብትን፣ ወሳኝነትንና አማራጭ መንገዶችን የሚያሳጣው የመሰተ-ፋቅር መንፈስ፤ አንደኛው የዲያብሎስ የውጊያ አቅጣጫ ነው። የዚህን መንፈስ ጥቃት በሴቶች በኩል እንዴት እንደሚፈጸም፤ በምሳሌ እንመልከተው።

በዘህ ዘመን ብዙ ሴቶች የትዳር ጓደኛ ለመያዝና ሀብት ለመሰብሰብ የሚጠቀሙበት አንዱ ዘዴ፤ በክፉ መንፈስ መሣሪያነት ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር መሞከር ነው። በዚህም በርካታ አባወራዎች በሚስቶቻቸው የመስተ-ፋቅር መንፈስ ታስረውና አዚም ተጭኗቸው ኑሯቸውን፣ ሀብታቸውንና ቤታቸውን የመምራትና የማዘዝ መብትና አቅም አጥተው፤ ከወዲህ ወዲያ ሲዋትቱ ይታያሉ።





ወንዶችም በተመሣሣይ መንገድ፤ እንደዚሁ በመንፈሱ ርዳታ ሴት እህቶችን ሲያደፃጡ ይታያሉ።

በደከሙበት፣ በለፉበትና ባለሙበት በሆኑበት ገንዘባቸው መወሰን ሳይችሉ ቀርተው፤ ለጫማ ማስጠረጊያ እንኳን ሳይቀር ሚስቶቻቸውን እየጠየቁና እያስፈቀዱ ጥገኛ በመሆን፤ ማንነታቸው ጠፍቶአቸው በመንፈሱ ተጽዕኖ ሥር ወድቀው፤ ፈዘውና ደንግዘው የመከራ ሕይወት የሚገፉ ጥቂቶች አይደሉም።

## የመንፈሱ አሠራር፤

ሚስት እንደባል በመሆን፤ በመንፈሱ አጋዥነት በባልዋ ላይ መብትን የሚያሳጡ ልዩ ልዩ ተጽዕኖ ታሳርፋለች። በዚሁ መሠረት፤ባል የሚስቱን ድምጽ ሲሰማ የሚደናገጥ፣ የሚርበትበትና እንደ ሰረቀ ሰው የሚሽቆጠቆጥ ከሆነ፤ እንዲሁም የእርሷን ፊትና ድምጽ እየተከተለ፤ አለአግባብ ስትስቅ የሚስቅ፣ ስትደሰት የሚደሰት፣ ስታዝን የሚያዝን፣ ስታለቅስ የሚያለቅስ፣ ወዘተ ... ከሆነ፤ በዚህ መብቱን በሚያጠፋው የመስተ-ፋቅር መንፈስ ተይዟል ማለት ነው።

ከሚስት አሉታዊ ስሜት መንጭተው በባል ላይ የሚያድሩና የሚያርፉ፤ የተወራራሽነትና የተመሣሣይነት ጠባይ ካላቸው የክፉው መንፈስ ተጽዕኖዎች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት፤

### ሀ. በገንዘብ፤ በተለይም በደመወዝ ላይ መብት ማሳጣት ፤

ባል ደመወዙን እንደተቀበለ እንዳለ ለሚስቱ እንዲሰጥ የተላከበት የመስተ-ፋቅር መንፈስ ከውስጡ ቁጭ ብሎ ያዘዋል። በዚህም የተነሣ በደመወዙ ላይ ሙሉ በሙሉ መብት ከማጣቱም በላይ፤ ልብስ፣ ጫማ ወዘተ... ሌሎች ቁሳቁስ ለመግዛት ከፈለገ፤ ፍጹም የሚስቱን ፈቃድ እንዲጠብቅና ዕድሜ ልኩን ራሱንና ቤተሰቡን በደመወዙ እየወሰነ እንዳይመራ፤ በአጠቃላይ የገንዘብን ጥቅም እንዳይረዳ፤ መንፈሱ ከባድ ጫና ያሳድርበታል።

ለ. <u>የባለቤትነት መብት፤ ማሳጣት</u>፤

የመሬት ይዞታ ባለቤትነት፣ የመኪና ሊብሬና የባንክ (ገንዘብ) ደብተር እንኳን ሳይቀር፤ ባል በስሙ ተመዝግቦ እንዲይዝ አይፈቀድለትም። ምናልባት ቀደም ሲል ከወላጆቹ በውርስ ወይም በሌላ መንገድ የተላለፈና የተያዘ በስሙ ያለ ሀብት ቢኖር እንኳን፤ በዚህ የመስተ-ፋቅር መንፈስ ሲያዝ፤ በመንፈሱ ድብቅ ሥነ-ልቦናዊ አሠራር በመተብተብና ልቦናውን በመስለብ፤ በፍጥነትና በድንገት እያቻኮሉ ይዞታውን ለሚስቱ ወይም ሚስቱ ለፈቀደችለት ሰው በማዛወር፤ ባዶ እጁን እንዲቀር ያደርገዋል።

ሐ. <u>ወሳኝነትና አማራጭ ማሳጣት</u>፤

በማንኛውም ሁኔታና የራሱ ጉዳይ ላይ፤ ያለሚስቱ ፈቃድና እውቅና ምንም ዓይነት ውሳኔ ላይ መድረስ እንዳይችል፤ በሕሊናው ማገናዘብም ሆነ መፈጸም እንዲሳነው፤ በራሱ እምነት እንዲያጣ፣ ሰይጣንና ሚስቱ ብቻ በኮድ የሚከፍቱትና የሚዘጉት ሰው ሆኖ፤ ያለሌላ አማራጭ እንዲኖር ውስጡ ባለው መንፈስ አስገዳጅነት ይታሰራል።

መ. <u>ዘመድ አዝማድን መርሳት</u>፤

ዘመዶቹ በተለይም እናትና አባቱን ለመርዳትም ሆነ ለመጠር የሚስቱን አዎንታ ካላገኘ፤ መኖራቸውንም እስከመርሳት ይደርሳል። እናትና አባትም ለልጃቸው የሚኖራቸው ግምት ከኩራት፣ ከጥጋብና ከትዕቢት የመነጨ አድርገው ስለሚወስዱት፤ በጨካኝነቱ እያማረሩና እየተበሳጩ፤ ‹‹ <u>የወላድ መካን ነን</u> ›› ብለው እንዲያዝኑበትና እንዲረግሙት፤ መንፈሱ መንገድ ይጠርግለታል።

ሠ. <u>የልጆችን ፍቅር ማጣት</u>፤

በመንፈሱ አሉታዊ ተጽዕኖ አባት ለልጆቹ የሚኖረው ግምትና አስተሳሰብም ሰለሚዛባና ስለሚዘበራረቅ፤ ልጆቹ የአባት ፍቅርን





ሳያውቁ ከማደጋቸው በተጨማሪ፤ አባታቸው ላይ ያለው ክፉ መንፈስ ከእናት የኃጢአት እርግማን ጋር ተጣምሮ <u>አብሯቸው ስለሚወለድ</u> ልክፍት ሆኖባቸው፤ ሕይወታቸው መከራ የተጠናወተው እንዲሆን ያደርጋል። በዚህም፤ ለአባታቸው የሚጸልዩት በሕይወት እንዲቆይ ሳይሆን፤ ሞቱን በመመኘትና እንዲፋጠን የሚለምኑ የእርግማን ልጆች ይሆናሉ።

## <u>መንፈሱን የሚልኩ ሰዎች ጠባይ</u>፤

እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ቶሎ የማይበርድ የጥቅም ፍላጎትና የትርፍ አምልኮት ያላቸው፣ ዝናንና ክብርን የሚወዱ፣ ሕይወታቸውና ኑሯቸው በጥድፊያ የተሞላ ቢሆንም፣ ሥልታዊ በመሆን በክፋት ጎዳና ላይ በጥንቃቄ የሚራመዱ፣ ትልቅነትን ለመቀዳጀት የማይቀብሩት ነገርና የማይቆፍሩት ጉድጓድ የሌላቸውና በዚህም ሥር የሰደደ ክፉ ፍላጎታቸውና ምኞታቸውም የተነሣ፤ ከጠንቋይና ከአስማተኛ አምባ ምንጊዜም የማይጠፉ ቤተኞችና ቤተሰብ የሚሆኑ ናቸው።

- በመልክና በውበታቸው በመመጻደቅም፤ የመንፈሱን የአሠራር ዘዴ በመጠቀም፤ ከባሎቻቸው አልፈው ሌሎች ወንዶችን እልህ ውስጥ በማስገባት፤ የሌላውን ሰው ሕይወትና ኑሮ ለመጉዳት በተለይም ሀብትና ንብረቱን ለመውሰድ ይንቀሳቀሳሉ።
- ሰውን ለማጥመድ፤ ሙሉ ስሜትን ለሌሎች ሰጠቶ በጥሞና በማዳመጥ፤ ጠባያቸውን ተለማማጭና አንደበታቸውን ደግሞ፤ ርቱዕና እጅግ የለሰለሰ፣ የጣፈጠና የሚያሳዝኑ ቃላት የበዙበት በማድረግ፤ከባሎቻቸው ውጭ ወይም በተጨማሪ፤ ሀብትና ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ፤ ያለይሉኝታ ሲራወጡ ብዙ ጊዜ ይታያሉ።
- በዋዛ ፈዛዛ የሚያባክኑት ጊዜ፤ ለሥራ ከሚሰጡት ጊዜ ይበልጣል። ሥራ ሠሩ ከተባለ፤ በተንኮልና በክፋት የተመላለሱበት መንገድ፤ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ይሆናል።

- መዘዛቸውንና ጡሳቸውን ለሌላ የሚያወርሱ፣ ጣልቃ ገብ ዓይንና ምላስ ያላቸው፣ ጠባያቸው ተለዋዋጭና ቅብጥብጥ በመሆኑ፤ምንጊዜም ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው።
- ብዙ ጊዜ በራሳቸው ጉዳይ ላይ ምስጢራዊ ከመሆናቸውም በተጨማሪ፤ በሃሳብ ሰጪነትና በመደመጥ ሁኔታ ላይ፤ ራሳቸውን ለማስቀደም ይጥራሉ። ሁሉም ቦታ ላይ አለሁ፣ አለሁ ማለት የሚወዱና በማንኛውም መንገድ ከሌሎች ሁሉ በልጦ ከፊት ለመገኘት የሚፈልጉ ናቸው።
- የትልቅነት ጠባያቸው፤ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ከሚጠቀሙበት ሥልት አንዱ በመሆኑ፤ ትምክህተኝነትና ገደብ የሌለው ባዶ የበላይነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል።
- በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አንፃር ሲታዩ ደግሞ፤ ከማንም ሰው በላይ ቀዳሚ ተጓዥና ገዳማዊ በመሆን፤ የማስመሰል ጠባያቸው የጎላ ነው። እውነታው ግን ፈጽሞ ከዚህ የራቀና በሕይወት ዘመናቸው የእግዚአብሔርን ቤትና ቅዱስ ቃሉን ለማፍቀርም ሆነ ለመስማት፤ ጨርሶ ሃሳብና ፍላጎት የሌላቸው መሆናቸው ነው።
- በጤናቸውም ረገድ፤ መንስዔውን በወል ሳያውቁት፤ ሁለንተናቸውን የታመሙና ምንጊዜም የቃተቱ ይሆናሉ። በትዳር ጓደኛቸው ላይ የላኩት መብትን የሚያሳጣው የመስተ-ፋቅር መንፈስ፤ ለጊዜው ጥቅም የሰጣቸው ቢሆንም፤ ውሎ አድሮ መንፈሱ መልሶ ራሳቸውን ሊጎዳቸው የሚችል መሆኑን ቢያውቁ እንኳን፤ በጥቅም በመታወር፤ የሚከተለውን ጉዳት አምኖ ለመቀበልና ለማገናዘብ ድፍረቱን ያጣሉ።
- ብዙ ጊዜ ተኝተውም ሆነ ቆመው የሚጨነቁ፣ እርካታ የሌላቸው፣ ግራ የተጋቡና የፈለጉትን ደስታ ሳያገኙ እየተበሳጩና እየተናደዱ አንዳንዴም፤ ለብቻቸው በር ዘግተው





እናት የምተባቸውን ያህል ሲያለቅሱ የሚታዩና የሚስተዋሉ ናቸው።

- በሰው ፊት ደስተኛ ለመምሰል የውሸት ፈገግታ ያሳያሉ፤ የውሸት ሳቅም ይስቃሉ። በአለባበስ በመሽቀርቀርና ከአንገት በላይ በሆነ የማስመሰል የአነጋገር ለዛ፤ የፊት ገጻቸውን በመለወጥ፤ ውስጣቸውን ለመሸፈን ይጥራሉ።
- በጠባያቸው ወግ አጥባቂዎች፣ ሥራ የሚወዱ ሰዎችን የሚተቹ፣ አቃቂርና የነገር ብልት የሚያወጡ፣ ጸጉር የሚሰነጥቁ፣ በተንኮልና በክፋት የተሞላ ልቦናና ሕሊና ያላቸው ናቸው።
- ጥቅማቸውን ለማስጠበቅና ለማስከበር ሲሉ፤ ቦታና ጊዜን የማይመርጡ፣ ርህራሄ ያልፈጠረባቸውና ለማንም የማያዝን ልብ ያላቸው፣ ሚዛናዊነትና ፍትሐዊነት የጎደላቸው፣ በብልጣ-ብልጥነትና በዓይን አውጣነት በድፍረት የሚንቀሳቀሱ፣ በጥቅም ማንንም ሰው የሚለውጡና አሳልፈው የሚሰጡ፣ ለሌላ ሰው ፈጽሞ የማይመች የተጋፊነት ጠባይ የሚታይባቸው፣ ብዙ ጊዜ በክህደት ረድፍ ላይ የሚገኙና የሚቆሙ፤ በከሳሽና በተከሳሽነት ፋይል፦ ምንጊዜም ከፖሊስ ጣቢያና ከፍርድ ቤት አካባቢ የማይጠፉ፣ ፍጹም አስቸጋሪ ሰዎች ናቸው።

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው፤ ትዳር ለመያዝ፣ <u>በተለይም ንብረትና ገንዘብ ለማጋበስ</u> ሲባል የሚላከው ይህ <u>የሕልውና መብትን የሚያሳጣው የመስተ-ፋቅር መንፈስ</u>፤ በሴቶች ላይ በምሳሌነት የቀረበ ይሁን እንጂ፤ <u>ብዙ ወንዶችም በተመሣሣይ መንገድ ሴት እህቶችን</u> በመንፈሱ በማሰር፤ ፍጹም ተገዢዎቻቸው ሲያደርጉ በወል ይስተዋላሉ።

**በአጠቃላይ** መስተ-ፋቅር «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» የሚለውን ቅዱስ ቃሉን የሚጻረር የዲያብሎስ አሠራር ነው።

## 1.6 ዓውደ ነገሥት - ወፍካሬ ከዋክብት (ኮከብ ቆጠራ) (አስትሮሎጂ)

‹‹ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፣ ሟርተኛም፣ ሞራ ገላጭም፣ አስማተኛም፣ መተተኛም፣ በድግምት የሚጠነቁልም፣ መናፍስትንም የሚጠራ፣ ጠንቋይም፣ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ።›› ዘዳግም 18÷10-11

ዓውደ ነገሥት በጥንታውያን የኢትዮጵያ ሊቃውንትና ጠበብት የተዘጋጀ፤ የሥነ-ምርምር ውጤት እንደሆነ የተገነረለት፤ ታላቅ ብሔራዊ ቅርስ ነው እየተባለም የሚሞካሽ፤ ነገር ግን እውነታው ከዚህ ጭብጥ ፈጽሞ የራቀ፤ ለዘመናት ያህል ተሸክመን የኖርነው አሁንም የተሸከምነው፤ ከሰይጣን ጋር አቆራኝቶ፤ የዲያብሎስ ልጆች እንድሆን ያደረገ የክፋው መንፈስ ሌላው መመሪያ ነው።

ትውልድን ያበላሸውና የሚያበላሸው፣ ያሳተውና የሚያስተው፣ ያጠፋውና የሚያጠፋው፤ በአጠቃላይ አገርና ሕዝብን ያወደመውና የሚያወድመው የሰይጣን መጽሐፍ፤ እንዴት ነው የሚያኮራ ብሔራዊ ቅርስ ሊሆን የሚችለው? እግዚአብሔር አምላክ ማስተወዋሉን ይስጠን።

ዓውደ ነገሥት፤ ለሚያምኑት ወይም ለተቀበሉት ሰዎች፤ የወደፊት ዕድላቸውን የሚያስምሩበት፤ ጥንዶች ጋብቻ የሚመሠርቱበት፣ የሥራ፣ የትምህርትና የእውቀት ወዘተ... ሥምረት ወይም ውድቀት የሚላክበት፣ የሚወለዱ ልጆች፣ ጠባይና አመል የሚለይበት፣ በሌላ አነጋገር፤ ከመናፍስቱ ጋር የሚኖራቸው ቁርኝት ወይም ግንኙነት የሚመዘንበትና የሚወሰንበት፤ የሰይጣን ዲያብሎስ የሥሌት መሣሪያ ነው።

የዓውደ ነገሥት ወይም የኮከብ ቆጠራ መንፈሶች፤ ለሰይጣን የመነሻ፣ መንደርደሪያ ጥቆማ የሚሰጡና የሚያቀርቡ፤ ሰዎችን





ከዲያብሎስ ጋር የሚያገናኙ፤ የክፋው መንፈስ የድርጊት የጊዜ ሠሌዳዎች ናቸው።

መናፍስቱ፤ በሰይጣን ኀታቹ ማለትም፤ በጠንቋዩ፣ በመተተኛው ወይም ደግሞ በራሳቸው በግለሰቦቹ አማካኝነት፤ የወደፊት ስሌታቸውና ውድቀታቸው፣ በዓውደ ነገሥቱ የስሌት ቀመር መሠረት እየተሠላ፤ እንዲሁም የእጅ መዳፋቸው እየታየና እየተነበበ፤ በጥንቆላው አሠራር አማካኝነት የሟርቱን ዓለም በወዳጅነት ይቀላቀላሉ።

በመጀመሪያ ይህ መጽሐፍ ሲገዛ፤ ቀጥሎም ሲገለጥ፤ በገዛውና በገለጠው ሰው ሕይወት ውስጥ ለመግባት፤ የክፋው መንፈስ ሠራዊት ዙሪያውን ይከባል። ለሥራ ይሰበሰባል፤ ተሰልፎ ይጠባበቃል።

‹‹ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራል።››
1ኛ ጴጥ፤ 5÷8

ዓውደ ነገሥት ቆጣሪና አስቆጣሪ ሆይ አስተውል!

‹‹ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ።›› ሮሜ. 2÷5